ይህ ቀን ማቆሚያ የለውም?

ነገር ግን ጀግኖቹ የሚያቆሙ አይነት አልነበሩም:: መጠለያ የለም፤ መሬቱ ሜዳማ ነው ሳሩም በእሳት ተቃጥሏል:: አማራጭ ስላልነበር ጣልያኖቹ መሬት ላይ ተጋድመው መተኮስ ጀመሩ:: ወድያውኑ ደግሞ ዘለው ይነሱና የሚችሉትን ያህል ነብሳቸውን ለማዳን ይሮጣሉ:: እንደዚህ እያደረጉ እየደጋገሙ የሚችሉትን ያህል ራቁ::

አቢሲኒያኖች ደግሞ ቀደም ብሎ እንደሆነው ሁሉ ትኩረታቸውን መኪናው ላይና ታንኮቹ ላይ አደረጉ:: ብዙ ጊዜም ሳይወስድ ቁጥጥር ስር አደረጓቸው *ሁለት የኢጣልያ ታንከኞች ብቻ አመለጡ::

ማሳደዱም ቀጠለ በዚያው ልክ ደግሞ ከጣልያኖች ጋራ የተሰለፉት የኤርትራውያኑ ጉብዝና የተሞላበት መከላከል እስከ ማይ ሚኒ ወንዝ ድረስ ቀጠለ:: እዚያ ሲደርስ ቆመ:: ምክንያቱም ጨለማው እየመጣ ነበር:: አቢሲኒያኖች ደግሞ ከዚያ በላይ መግፋት አልቻሉም:: ምክንያቱም የአንዳ ስላሴ የጠላት ካምፕ ማዶ እንዳለ ያውቁ ነበር::

ያን ቀን ከረፋዱ በኋላ  የጠላት ቦምብ ጣይ አውሮፕላን በጦር ሜዳው ላይ እያንዣበበ ትንንሽ ቦምቦች እየጣለ አውቶማቲክ መሳሪያም ይተኩስ ነበር:: አቢሲኒያኖች ደግሞ ከጠላት ጋራ ግብግብ ይዘው ጉዳይም አልሰጡትም ነበር:: ተቀላቅሎ ስለነበር ለቦምብ ጣይ አውሮፕላኑ ጠላትና ወዳጅ መለየት ስላልቻለ ብዙ ጉዳት አላደረሰም:: በኋላ  ግን የአቢሲኒያኖች ስንቅና ትጥቅ ክፍሉን አግኝቶ ብዙ ጥይትና ሌላም ጓዝ በእሳት ቦምብና በሚነደው ሳር ምክንያት ከጥቅም ውጭ ሆነ::

---

** ያን ቀን ካመለጡ የኢጣልያ ወታደሮች አስራ አለቃ ብሩኖ የሚባል እነደነበረና ታንኮቹን የሚይረቡ ናቸው ብሎ እንዳማረረ ተጠቅሷል:: አስር አለቃው በአካባቢው ከነበሩ የሊቢያ ስፓሂ ወታደሮች ጋር እንደተደባለቀ ተዘግቧል::*
*Amedeo: A True Story of Love and War in Abyssinia. Sebastian O'Kelly*

*ከዚህ ፅሁፍ ታሪክ በመነሳት ከጣልያኖች ጋራ የመጀመሪያውን ጦርነት ያካሄዱት የደጃዝማች አያሌው ተከታዮች ከሆኑ፤ በዚህ ጦርነትም ታንክ የተደመሰሰበት ከሆነ፤ የመጀመሪያውን ታንክ የማረከው የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ባላምባራስ ተሰማ መሆኑ ነው:: ይህንን ግን አንባብያንና የታሪክ ባለሙያተኞች በአዎንታ ሆነ በአሉታ እንዲነጋገሩበት እንጋብዛለን::*



# ምዕራፍ አሥራ ሁለት

## ቁስለኞችን ማከም

በታህሳስ ስድስት በእንዳባጉና የተደረገው ጦርነት ምዕራቡን የትግራይ ክፍል ከጣልያኖች ቅኝ ግዛት አሰለቅቋል:: ገና በስቲት አካባቢ ነው የተባለው ግን ድንገተኛና ህይለኛ ጥቃት ያካሄደው የአቢሲኒያ ጦር ሌሎች በአዲያቦ፣ ሽሬ እና ዛና የሚገኙ ስድስት የጣልያን የጦር ካምፖችን አስጊ ሁኔታ ፈጥሮባቸዋል:: ስለዚህ ጣልያኖቹ በሰባት ማታውኑ ጓዛቸውን ጠቅልለው በጥንቃቄ ወደ ዋናው ካምፕ አክሱም ገቡ::

በአቢሲኒያኖች በኩል የደረሰው ጉዳት ግን ከፍተኛ ነበር:: ሶስት መቶ ስማንያ ሁለት ሰዎች ተወዳጁንና ጀግናውን ፊታውራሪ ሽፈራውን ጨምሮ ሞተዋል:: ሁለት መቶ ሃምሳ ስድስት ሰዎች ደግሞ ቆስለዋል::

አቢሲኒያኖቹ ስህይወት ስለማይሳሱ ከተገኘው ውጤት ጋራ ሲወዳደር ጉዳቱን የከፋ አላደረጉትም:: በችኮላና በድንቁርና ታንኮችን ባያጠቁ ኖሮ የደረሰው ጉዳት ከዚህ ያንስ ነበር :: ያም ሆኖ በዚህ ሁኔታ ትልቅ ድል ነው ያገኙት ለድፍረት የሚሆን የጦርነት ልምድም አገኙ:: እነዚህ ጭራቆች (ታንኮችን ማለት ነው) ሊደፈሩ የሚችሉ መሆናቸውን ተገነዘቡ::

በጣልያኖች በኩል ደግሞ ሰባት መኮንኖች፣ ሃያ ሶስት ነጭ ወታደሮች፣ አርባ ስምንት የኤርትራ ተወላጆች መኮንኖችና መቶ ሃያ ሰባት ባንዳ ወታደሮች ሞተውባቸዋል:: የቆሰሉት ቁጥር ሰላሳ ብቻ ነው ተብሎ የተዘገበው::

የዚህ የተሰጠው ቁጥር አጠራጣሪ ነበር ምክንያቱም ሃምሳ አንድ የነጭ ወታደሮች ሜዳው ላይ ሞተው ተገኝተዋል:: ስንቶቹ መኮንኖች እንደሆኑ ማወቅ አይቻልም ነበር:: ምክንያቱም ልብሳቸው ስለተውሰደ ራቁት ነበሩ:: ልብስ በጣም ተፈላጊ ነበር::

ሁሉም ሞተው የተገኙት አቢሲኒያውያን የጦርነቱ ስት ማምሻውን እጠገብ ባለ ቤተክርስቲያን በዘመድና ወዳጃጃቸው ተቀበሩ::

የፈታውራሪ ሽፈራው የንስሃ አባት ከዚያ ወዲህ አልታዩም። የተወሰኑ ወታደሮችን የፈታውራሪ ሽፈራውን አስከሬን እንዲጠብቁ ከጠየቁ በኋላ ጦርነቱን ተቀላቅለው በዚያው ወድቀዋል።

ብዙ ንብረት ደግሞ በድል አድራጊዎች እጅ ወድቋል። ሰባት ታንኮችና አራት መኪኖች ብትንትናቸው ቀርቷል። ሁለቱ ስለተገለበጡ ማንቀሳቀስ አልተቻለም። ሶስተኛው ግን እጠገብ ወዳሰ ሰፈር ተወስዶ የአሥራ ዘጠኝ አመቱ ጣልያናዊ እንዲነዳው ተገዷል። ማራኪዎቹ የተማረከውን ወታደር ይዘው በሰፈሩ ላሉ ሴቶች በማሳየት እየተዝናኑ ነው። ይህ እስፈሪ ብረት እየተንኳኳ በሰፈር ሲያልፍ ያዩ ሴቶች ጀግኖቻቸውን በእልልታ ተቀበሏቸው።

አንድ የግል አውቶሞቢልም በከፊል ተጎድቷል። መኪናው የራሱ ታሪክ አለው። የቆየ የፎርድ መኪና ሞዴል ቲ በስዊድን ዋና ከተማ ሰቶክሆልም የተገዛ ነበር። ሚሲዮናዊ አባ እንደርሰን መኪናውን በመላ አውሮፓ ኢጣልያ ድረስ ከቤተሰቦቹ ጋራ ነድቶ ከወሰደው በኋላ በመርከብ ወደ ግብፅ አሰልኮ ከግብፅ ደግሞ እየነዳ ወደ ኤርትራ ይዞ ዘልቋል። በኋላም ወደ አድዋ እንዲዛወር ሲታዘዝ መኪናውን እስከ ደንበሩ ድረስ እየነዳ መጣ፤ ከዚያ በኋላ መንገድ ስላልነበረ ማቆም ነበረበት። በዚያን ጊዜ አዛዡ ራስ ሰዩም መንገድ እንዲሰራ ትዕዛዝ ሲሰጡ "ያማ በማዕከላዊው መንግስት በአዲስ አበባ ከልክል ነው" ተባለ።

የቫይኪንግ ደም ያለበት አባ አንድርያስ ግን በዚህ ማቆም አልወሰነም። ስለዚህ ሰዎች መኪናውን እንዲሸከሙ ጠየቀና ከአካባቢው ወደ ሺ የሚቆጠሩ ገበሬዎች ተሰበሰቡ። ሃምሳ ኪሎሜትር የሚሆነው መንገድ በሚጮሁና በሚዘፍኑ ገበሬዎች ትከሻ ከተጓዘ በኋላ የመጀመሪያው መኪና አድዋ ውስጥ በዚህ መልክ ገባ።

ይህ ታሪክ እየተነገረን በሰፊው ጦርነት በተካሄደበት መሬት አቋርጠን አለፍን። ብዙ ጊዜ ነው የወሰደብን። ብዙ ጊዜ ደግሞ ከኢጣልያ አውሮፕላኖች መደበቅ ነበረብን። በየቦታው ሬሳ ነበር። በቅሎና ፈረስ ግመልን ጨምሮ ከጥቁርም ከነጭ ሰው ሬሳ ጋር ተደባልቆ ወድቋል። አቢሲኒያኖች ጠላቶቻቸውን አይቀብሩም በተለይ ከነሱ ውጭ ሌላ ዝርያ ወይም ሌላ ሀይማኖት ከሆነ።

የሚቀፍ ሽታ አየሩን ሞልቶታል



የመጨረሻውን ታንክ እንዳየን ወደ ደቡብ አቅጣጫ መንገዳችን ቀይረን የቆሰሉ ወታደሮች ወዳሉበት ካምፕ ሄድን። ቦታው ልንደርስ ትንሽ ሲቀረን ከጫካው መሀል ጎራዴ የያዘ ሰው ድንገት እየሮጠ ወደኛ መጣ

"አሃ! እኛ በእግራችን እየሄድን ይሄ እሳማ በፈረስ ይሄዳል? አሳየዋለሁ! አሳየዋለሁ!!" ጣልያናዊ ነው የመሰለኩት፤ ከዛም በላይ አስረኛ

ወድያውኑ ሽጉጤን መዘዝኩ

"የታጠቀ አስረኛ ነው እንዴ ይዛችሁ የምትዞሩት?" አለ በመገረም

ቀኛዝማች ንጋቱ በመሀከላችን ገቡና ማን እንደሆንኩ ነገሩት። ሰውየውም ጉልበቴን ሳመና ይቅርታ እንዳደርግለት ጠየቀ። ሰው እንዴት አድርጎ ነው ከነዚህ አይነት ያዋቂ ልጆች ላይ ቂምስ ወይም ጠላትነት የሚይዘው?

ካምፑ ውስጥ ስንገባ የቁስለኛው ካምፕ ማለት ነው ሽማግሌው ፊታውራሪ ነጋሽ ከነበሩበት ዋሻ ውጥተው ተቀበሉኝ። የጣልያን የወታደር የብረት ቆብ እናታቸው ላይ አድርገዋል፤ ቆቡ ላይ የተፃፈውን ምልክት ሳስተውል አዩኝና

"ይህ ብረት ቆብ የጣልያን ጄኔራል ነው በምልክቱ እንደምታየው፤ ከጄ ሳያመልጥ ደርሼ ጉሮሮውን ቆረጥኩት"

የጄኔራል ነው የተባለውን ምልክቱን ሳየው የሬድዮ ሠራተኛ ነው የነበረው ነገር ግን ነገሩን ላለማበላሸት ስል ሰውየውን እንኳን ደስ አለዎት አልኳቸው።

ዋሻው ውስጥ ምግብ ተዘጋጅቶ ነበር። ብዛት ያለው የአተር አሸት አምጥተው ፊታችን አስቀመጡ። አተሩን እየፈለፈልን ስንበላ ሽማግሌው ነጋሽ ሀሳብ የገባቸውና የተጨነቁ ይመስላሉ። ምን እንደሚያስጨንቃቸውም ጠየቅኋቸው።

አንድ ያላቸው ልጅ በፅኑ ቆስሏል

"ለምን ቀደም ብለው አልነገሩኝም?"

"ትንሽ እረፍ ሳትል ላስቸግርህ አልፈለግሁም"

ወዲያውኑ ወደ ቆሰለው ሰውየ ሄድን። አሳዛኝ ሆኖ ልጃቸው የመጨረሻ ሰአቱ ላይ እንደነበረ ግልፅ ነው። እንደቆሰለ ብዙ ደም ስለፈሰሰው ደክሟል። ደሙም መመረዝ ጀምሮአል። ማድረግ የምንችለውን ሁሉ አደረግን ሌላው ቢቀር ጥሩ አልጋ ላይ አርፎ ነበር።

ጥቂት ቆይቶ ደግሞ ቁጥራቸው በርከት ያሉ ሰዎች በዋሻው መግቢያ በር ላይ ተሰበሰቡ። ሐኪሙን ማየት ይፈልጋሉ። መልኩ ምን እንደሚመስል የፀጉሩ ቀለም፤ ትልቅ ነው ወይስ ትንሽ፤ ደግሞስ ምንድንው የለበሰው?

የመሳሰሉት:: በመልኩ ማወቅ ይፈልጋሉ ምክንያቱም በኋላ ቁስለኞች አከባቢ ሲሄድ ሰው እንዳይገለው ነው:: ቁመቴ(የዶክተር ናየሰተሮም ቁመት ስድሰት ጫማ ከሁለት ኢንች ነበር) ለመለየት ይረዳቸዋል፤ ምክንያቱም በነሱ አስተሳሰብ ጣልያኖቹ ቁመታቸው አጭር ነው:: በራሳቸው ቋንቋ መናገር ስጀምር በመሃከላችን የነበረው መከለያ ተወገደ እና እንደወንድማቸው አድርገው አዩኝ::

ሁሉም ዋሻዎችና ቁጥቋጦዎች በወታደሮች ስለተያዙ ለኔ ማረፊያ የሚሆን ቦታ ማግኘት አስቸጋሪ ነበር:: ውነት ነው ብዙዎቹ አብሬያቸው እንድሆን ጋብዘውኝ ነበር ግን በብዙ ምክንያቶች ይቅርብኝ ብያለሁ:: በመጨረሻ ሜዳ መሀከል ላይ ወዳለ ባዶ የገበሬ ቤት ለመሄድ ወሰንኩኝ:: ሶስት በጥሩ ሁኔታ የነበሩ ጎጆዎች ነበሩ:: ሶሰቱን ለመኖርያ፤ ለእቃ ማስቀመጫና ለማከሚያ ቦታ ማድረግ ይቻላል:: በተጨማሪ ያስተዋልኩት ነገር ቢኖር የኢጣልያ አውሮፕላኖች የሚጠረጠር ነገር ካላዩ በሰተቀር ጎጆዎች ላይ በምብ አይጥሉም ነበር::

በቅጠል የተሰራ ጎጆ ቆመ ለታካሚዎች እንደመቆያ ከፍል መሆኑ ነው:: ሰዎች ከፊት ለፊት ሜዳ ላይ እንዳይሰባሰቡ ዘቦች እንዲቆሙ ተደረገ:: መሀል ጦርነት ላይ ሰላለሁ የቀይ መሰቀል ባንዴራ መሰቀል ትክክል ነው ብዬ አላሰብኩም እንዲያውም ለኢጣልያ አውሮፕላኖች የኢላማ ምልከት መሰጠት ይሆናል::

እንግዲህ በዚህ ሁኔታ አውሮፕላኖችን ሳልፈራ መድፈሬ በአንዳንድ ወታደሮች ዘንድ ደፋር ሰው የሚል ሙገሳ አስገኝቶልኛል በሌሎች ዘንድ ግን ከምኝ ነው የተቆጠርኩት:: በቀን ብርሃን ሰላሳ ሰዎች ብቻ ደፍረው ለህክምና መጡ በዚህ ምክንያት ሥራዬን በሚከተለው ሁኔታ አደላደልኩኝ::

1. የመጀመሪያ የታመሙ ሰዎች ማያ ጊዜ ከጠዋቱ 11 ሰአት አስከ ጠዋቱ 1 ሰአት ድረሰ
2. ከአንድ ሰኣት አሰከ ጠዋቱ አራት ሰአት ማረፊያ ጊዜዬ፤ በዚህ ሰአት ቁርሰ የምበላበት፤ የህክምና መሳሪያዎችን የምቀቀልበት እና ለሚቀጥለው ሥራ ከሊኒኩን የማዘጋጅበት ጊዜ ነው



3. ከአራት ሰአት እሰከ እኩለ ቀን ሰድሰት ሰአት መንቀሳቀሰ የማይችሉ በየዋሻው ያሉ ቁሰለኞችን እየዞርኩ የምጎበኝበትና ቁሰላቸውን የማከምበት
4. ከሰድሰት ሰአት አሰከ ዘጠኝ ሰአት የምሳና የእረፍት ጊዜ
5. ከዘጠኝ እሰከ ምሽቱ አንድ ሰኣት ህሙማን የሚታዩበት ጊዜ፤ ከዚያም ቀጥሎ አሰከ ምሽቱ ሶስት ሰአት ተጨማሪ ሕሙማን የሚታዩበት ጊዜ ሆነ

ሁለት ትልልቅ ፋኖሶች ቀዶ ህክምና ለማድረግ በቂ ብርሃን ይሰጡ ነበር::

ለብቸኛ ዶክተር ከሶስት ያገሩ ተወላጅ ረዳቶች ጋራ ብቻ መሥራት የሥራ ጫናው በጣም ከባድ ነበር:: ሁሉን የሚያስፈልግ ነገር ለማድረግ አስቸጋሪ ነበር:: በተጨማሪ በቂ እንቅልፍ ማግኘት አልቻልኩም፤ በማረፊያ ሰአቶች መተኛት ብፈልግ በጣም ታሟል በሚባል በሽተኛ ምክንያት እቀሰቀሳለሁ:: በቀን እንዳልተኛ ደግሞ በአውሮፕላኖቹና በቦምቦች ፍንዳታ ድምፅ ድንገት አነቃለሁ::

ያም ሁሉ ሆኖ ብዙ የሚያስገርሙ ብዙም የሚያሰቁ ሁኔታዎች ስለነበሩ ብቸኝነቱ እንደሚቻል እንዲሆን ረድተዋል::

ለምን እንደሆነ በማይገባኝ ምክንያት በመትረየስ ጥይት መቁሰል እንደክብር ይቆጠር ነበር:: እኔ ቁሰሉ ከጠመንጃ ነው ወይም ከቦምብ ፍንጣሪ ነው ብዬ ብናገር ከሰድብ ነበር የሚቆጠረው:: ሐኪሙ ምንም አያውቅምም አባላለሁ:: ቁሰሉ ከመትረየስ አይደለም ብዬ ከተናገርኩ አንዳንዶች መታከሙን እምቢ ይላሉ ወይም ተከታታይ ህክምና አያደርጉም ::

አንድ ሰው በፍንጣሪ ተመቶ የተለያየ ሰውነቱ ከፍል ላይ አሰር ቦታ ቆሰሏል:: ሳላሰበው ሰውየውን "እድለኛ ነህ እንኳን በምቡ ወደ አየር አልወረወረህም" ሰለ በጣም ተናደደ:: "አታይም እንዴ? ይሄ ሁሉ ቁሰል በመትረየሰ ጥይት እንደሆነ አንዱ በዚህ በኩል ነው የገባው" አለ በቀኝ ትከሻው በኩል ወዳለው ቁስል እያሳየ “ይኸውና የወጣው ደግሞ በዚህ በኩል ነው” ብሎ በግራ ጭኑ ላይ ያለውን ቁሰለ አሳየኝ::

መከራከሩ ፋይዳ የለውም አቆሳሰሉ እንዳሰበውና እንደሚያምንበት እንደሆን ቢሆንለት ቶሎ እንደሚድንም አውቃለሁ::

ሰዎች የመግቢያና የመውጫ ቁስሎች ምን እንደሚመስሉ በደንብ ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡ ነገር ግን የመግቢያ ቁስል በጀርባቸው ከሆነ ለምሳሌ የአግራቸው መጫሚያ ሳይ፤ ታፋቸው ሳይ ሆኖ ሳገኘው ከዚያ በኋላ መግቢያና መውጫውን መናገር ያቆማሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ሲሮጡ ወይም ሲሸሹ ከኋላ የተመቱ መሆናቸውን በፍፁም ሊያምኑልኝ አይችሉም፡፡

በሙቀቱና በአፈር ምክንያት እኔ ከማከሜ በፊት ሁሉም ቁስሎች በበሽታ ይለከፋሉ፡፡ ባስኝ መሳሪያ ብዙም ማድረግ የምችለው ነገር ስላልነበር ቁስሉን ደም በያዘ መርፌ እየወጋሁ ማከም ባልጀምር ኖሮ እጄ እንደታሰረ ነበር የምቆጥረው ፡፡ ይህም ማለት በቁስሉ ዙሪያ የሚቻለውን ያህል ደም በመርፌ ይወጋል፤ ይህ ደግሞ በሽታው ከቁስሉ ውጭ ወደ ሌላ ቦታ እንዳይሰራጭ ይረዳል፡፡ ደሙም የሚወሰደው ወይ ከበሽተኛው ከራሱ ወይም ከሌላ ሰው ነው፡፡ በሽታው ከሰውነት አልፎ ወደ ሰውነት የተሠራጨ ከመሰለኝ ደግሞ ከሰውነት ወደ ሳይ ከፍ ብየ ወደ እጢዎች የሚመላለሰውን ፈሳሽ እዘጋለሁ፡፡

በዚህ አሠራር ምክንያት የሚገኘውን ያልተጠበቀ ውጤት ማየት አስደናቂና ደስ የሚያሰኝም ነበር፡፡ ከሀያ አራት ሰአታት በኋላ የቁስሉ ዙሪያ ጠቆር ያለና ሰማያዊ ባለው ቀለም ይተካና የቁስሉ ዳር የሚገኘው የሰውነት ክፍል ተከልሎ ይደርቃል፤ ከሁለት ወይም ሶስት ቁስል ህክምና በኋላ መርገፍ ይጀምራል፡፡ በተቃራኒው ግን በሞተውና በደረቀው ቦታ ከፍተት እንደሚፈጠር ወይም ደም መፍሰስ እንደሚጀምር ውነት ነው፡፡ ነገር ግን ቁስሉ ንፁህ ይሆንና እስቀያሚ ሽታውም ይጠፋል፡፡ ቁስሉም በቶሎ ይድናል፡፡

ይህ የህክምና ዘዴ ግልፅ ባይሆንም ሥራው ግን ቀላል ነበር፡፡ ሀያ ሲሲ ሲሪንጅ ከረጅም መርፌ ጋራ ነው የሚያስፈልገው፡፡ ደሙ በሰሪንጁ ውስጥ እንዳይረጋ ሶድየም ሳይትሬት የሚባል ፈሳሽ ጠብታ ይደረጋል፤ ከዚያ መርፌ አወጋጉ ልምድና ችሎታ እንደሚጠይቅ ግልፅ ነው፡፡ መርፌ ሲወጋ በሚፈጠረው እብጠት ምክንያት ለመጀመሪያዎቹ አስር ደቂቃዎች ሕምም ይኖረዋል፡፡ ነገር ግን ህክምናው ለበሽተኛው የሚጠቅም መሆኑን የተረዳ ሀኪም ከጩኸቱና ዋይታው ጆሮውን ደፍኖ ይሰራል፡፡ በአብዛኛው ጊዜ ማደንዘዣ መስጠቱ አስፈላጊ እንደማይሆን ነው የምረዳው፡፡ በአንድ አጋጣሚ እኔው ራሴ ይህንን የደም መርፌ መውሰድ ስለነበረብኝ እንዴት እንደሚያም በቀጥታ አውቀዋለሁ፤ ነገር ግን ሰው ሲቋቋመው የማይችል ነገርም እልነበረም፡፡



መዝገቤ ስለጠፋብኝ ስንት ሰው በደም መርፌ እንዳከምኩ በትክክል ቁጥሩን መናገር ባልችልም ከሰማንያ በላይ ለመሆናቸው ግን እርግጠኛ ነኝ፡፡ ከእስር በታች በሚሆኑት ህክምናው አልሰራም፤ ወይም በተሳሳተ መርፌ እሰጣጥ አለዚያም ደግሞ በሽታው በሰውነታቸው ከቁስሉ አልፎ በመሠራጨቱ ነው፡፡

በሽተኞቹ ራሳቸው ይህ የህክምና ዘዴ ጥሩ ነው ብለው ስላመኑ ብዙዎቹ እንዲሠጣቸው ይጠይቁ ነበር፡፡ ብዙዎቹ የቆሰሉ ሰዎች "የደም መርፌ" ይሰጠን ብለው ይጠይቃሉ፡፡ በሚጠይቁበት ጊዜ ይህ ህክምና እንደሌላው ህክምና ሁሉ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ብቻ ነው የሚሠጠው ብዬ የማቀርበው መልስ እያረካቸውም፡፡

በአራተኛው ቀን በእንዳባጉና የቆሰሉ አንድ ግራዝማች አመጡልኝ፡፡ ጦርነቱ ላይ ሰዎቻቸውን ለማበረታት "እይዞህ" እያሉ ሲጮሁ ጥይት በቀጥታ በተከፈተው አፋቸው ውስጥ ገባ፡፡

ጉንጮቻቸው ከንፈራቸው ጠቅላላ ፊታቸው አብጧል፡፡ መናገርም አይችሉም፡፡ አፋቸውን በከፈቱ ቁጥር የሚያጥወለውል ሽታ ይወጣል፡፡ ጥይቱ በቀኝ ጉንጫቸው በኩል ገብቶ በግራ ጉንጫቸው ወጥቷል፡፡ ጥይቱ ያለፈበት ቦታ ከፍተት ፈጥሯል፤ ቁስሉ የድርቀት ምልክት ያሳያል፡፡ ምላሳቸው በአግድሙ ተተርትሮ ቆስሏል፤ ጥርሳቸው ግን አልተነካም፡፡ አፋቸውን መነማመጥ ስለማይችሉ በሳዩ መጥፎ ሽታ ያለው ሽፋን የመሰለ ነገር ተጋግሮበታል፡፡

ለእኔ ወዲያውኑ ግልፅ የሆነልኝ ነገር ግራዝማቹ የመጀመሪያው የደም መርፌ ህክምና የሚደረግላቸው ሰው መሆናቸው ነው፡፡ ስለህክምናው ቀኛዝማቹን ነገርኳቸው፡፡ መርፌ ወግቼ በቁስሉና በአካባቢው ባለው ሰውነት ክፍል መሀከል ጥሩ የደም መከለያ ከማበጀቴና በንፁህ መሸፈኛ ጨርቅ ቁስሉን ከመሸፍን ውጭ በዚያ ቀን ይሁን በተከታታይ ቀን ሌላ ያደረግሁት ነገር አልነበረም፡፡ ጉንጫቸው ሳይ ስነበረው ቁስል ሌላ የተጠቀምኩት ህክምናም አልነበረም፡፡ አፋቸው ውስጡ በደንብ ተጠረገ ምላሳቸው ሳይ ያለው ቁስል በደንብ ተጠረገና የምላሱ ቁስል በመርፌ ተሰፋ፡፡ ከዚያ በኋላ በጥንቃቄና በትግስት እፋቸውን ማጠብ ቻልን፡፡

ለበሽተኛው የመጀመሪያው ቀን አስቸጋሪ ነበር፡፡ ጉንጮቻቸው ከመጠን በላይ አብጠው ነበር፤ በመርፌ የተሰፋው ምላሳቸውም ህመም ነበረው፡፡ መናገር አይችሉም ነበር ግን ቁጣ ከተመላበት አመስካከታቸው እኔ እንደገባኝ

ከሆነ እኔን እንደ ትልቅ ጅል ነው ያዩኝ፡፡ ከነበራቸው ህመም በተጨማሪ ነካከቼ ሁኔታውን አባብሼዋለሁ ማለት ነው፡፡ ለማስረዳትና ለማረጋጋት ያደረግሁት ሙከራ አልተሳካም፡፡ በብዙ ምክንያት ሞርፊን የተባለ የህመም መቆጣጠሪያ መድሃኒት ልሰጣቸውም አልደፈርኩም፡፡

በሁለተኛው ቀን ጠቅላላ ሁኔታቸው የተሻለ ሆኖ ታየ፡፡ ከሳምንታት በኋላ ቁስሉ ሁሉም ዳነ፡፡ ይህ ደግሞ ሁላችንም ያስደሰተ ነገር ነበር፡፡ ጉንጮቻቸው ላይ ቀለል ያሉ ሁለት ጠባሳዎች ነበሩ፤ ነገር ግን ያን የነበረውን ሁኔታ የሚገልጥ ሌላ ምልክትም አልነበረም፡፡ ንግግራቸውም ሙሉ በሙሉ ተመለሰ፡፡ በደም መርፌ በመስጠት ጥሩ ውጤት ካገኘሁባቸው አንዱ ይኸው የቀኛዝማቹ ቁስል ነው፡፡

ንጉሡ የቆሰሉት በሙሉ በሶስት ደረጃ ተከፍለው እንዲመዘገቡ ትዛዝ ሰጥተዋል፡፡ ቀለል ያለ ቁስለት፤ መካከለኛ እና ከባድ ቁስል፡፡ የመጨረሻዎቹ ማለትም ከባድ የመቁሰል አደጋ የደረሰባቸው ሽልማት አንድ ጊዜ በሚሠጥ ገንዘብ መጠን ወይም ጡረታ ይሠጣቸዋል፡፡ ይህንን ደግሞ ሁሉም ወታደሮች ጠንቅቀው ያውቁ ነበር፡፡ እንግዲህ ቁስሉ ትንሽ ሲሆን ጩኸቱ ግን ከመጠን በላይና የሚረብሽ ይሆናል፡፡

"ሀኪም መሞቴ ነው! ሀኪም በጠና ነው የቆሰልኩት ሊገለኝ ነው! ሀኪም አንዳሻህ አድርገኝ! እጄን ቁረጠው ጉሮሮዬንም ጨምረህ ቁረጠው፡፡ ተበላሽቻለሁ!" ይህን የመሰሉ ጩኸቶች ከጥዋት እስከ ማታ ድረስ እሰማ ነበር፡፡

ቀደም ባሉ በአቢሲኒያ በተደረጉ ጦርነቶች የቆሰለ ሰው ወደ ቤቱ እንዲመለስ ይፈቀድለት ነበር፡፡ ከቆሰለ ለሱ ጦርነቱ አበቃ፡፡ እሁን ግን ጥብቅ ትዛዝ ተሰጥቶ የቆሰሉት በሙሉ አዛው ግንባር ላይ እየታከሙ ሲሻላቸውና ሀኪም መዋጋት ይችላሉ ሲል ወደ ጦር ሜዳ እንዲመለሱ ይደረጋል፡፡

አንድ ቀን ከአዛዡ ከደጃች አያሌው ጥያቄ መጣ፡፡ አንድ ፊታውራሪ ወደ ቤቱ ተመልሶ ይሆን? ነገር ግን ደጃዝማች ደግሞ ይፈልጉታል፡፡ ይህ የተባለው ፊታውራሪ ብዙ ጣጣ አድርሶብኛል፡፡ ቁስሉ ቀለል ያለ ቢሆንም አልዳነም፡፡ አንዲህ እይነት ቀለል ያለ ቁስል ባለቸው ሰዎች ላይ ግራ የሚያጋባ ሁኔታ በግማሾቹ ላይ አስተውያለሁ፡፡ ቀላሉ ቁስል እንዴት ቶሎ አይድንም ነው ጥያቄው፡፡ ድሬሰሩ የሚያደርገውንም ነገር ጠጋ ብዬ በደንብ ተመለከትኩ ነገር ግን አእምሮየን በመላምት ሆነ በምርመር መልከ ብወጥረውም መልሰ ማግኘት አልቻልኩም፡፡



ድሬሰሩ ፈጠነ ፊታውራሪው ቁስሉን ለረዥም ጊዜ ያላስጠረገ ወይም ያላሳከመ መሆኑን አሲታወለኝ፡፡ ወደ ዋሻው ሄጄ ቁስሉን ማየት አለብኝ አልኩኝ፡፡ የተለያዩ ምክንያቶች እያቀረበ እምቢ ለማለት ሞከረ እኔ ግን ድርቅ አልኩኝ፡፡

ቁስሉ የተሸፈነበት ጨርቅ ሲፈታ ቡናማና ግራጫ መልከ ያለው ነገር ከቁሰሉ መሀል ላይ ተከምሮ እየሁኝ፤ ከለሩ ደግሞ አረንጓዴ ቀለም ያለው መግል መውረድ ጀመረ፡፡ ቁስሉ ደግሞ ከነበረው መጠን በአራት እጥፍ ጨምሯል፤ ቁሰልን እየበላ የሚያሰፋ ኬሚካል ያለበት ይመስላል፡፡

ምንም መጠየቅም አላስፈለገኝም፡፡ የችግሩ መንሰኤ ገብቶኛል፡፡ ቁሰል የሚበላው መድሃኒት ከሆነ ሥር ነው የሚዘጋጀው ሰሙን ግን አላውቀውም፡፡ ከቅቤና ከማር ጋር አንደ እጅ ከሁለት እጅ በሆነ መንገድ ተለውሶ ሲደረግ ቁሰል እንዳይድን የማድረግ ችሎታ አለው፡፡

እነዚህ ወሮበሎች በአፍንጫዬ እየንተቱ ሲያዞሩኝ ለንብተዋል፡፡ ጥያቄው ደግሞ ማነው የሚረዳቸው? ነው፡፡


ለካሰ ወጌሻው ነበር፡፡ ለኔ አንኳን እንደ ሥራ ጓደኛ ማለት ነበር የማላውቀው ሰውም አልነበረም፡፡ በፊታውራሪ ነጋሽ አርዳታ ተይዞ አንዲቀመጥ አሰደረግሁኝ፡፡ ችሎት ቀርቦ ሰንሰማ እያንዳንዱን ሰው በዚያ ሁኔታ ለማከም እምሰት አምሰት ማርትሪዛ ያስከፍል ነበር፡፡ የወሰደው ገንዘብ እንዲመለሰ ተደረገና ሶሰት ሰዎች ዋሰ ጠርቶ ሁለተኛ ካምፑ ወሰጥ ፊቱን እንዳያሳይ ተደረገ፡፡

ሌሎች በጠና የቆሰሉ የሞቱም ብዙ ነበሩ፡፡ አገጫቸው ብትንትኑ የወጣ፤ ፊታቸውን መለየት አስከሚያቅት ድረሰ የቆሰለባቸው፤ ምንም መሳሪያ ሰላለነበረኝ ያለአማራጭ እኔ ራሴ እጅና እግራቸውን የቆረጥኩባቸውን ይጨምራል፡፡

አንደነዚህ አይነቱ ቁሰለኞች ላይ ይህን ሁሉ ጉዳት ባደረሱ ሰዎች ላይ ምርር ያለ የጥላቻ ሰሜት ይፈጥርብኛል፡፡ ሥልጣኔ ነው ተብሎ ንብረት ለመዝረፍ ጥማት ያለበት ጉልበተኛ ደካማውን የሚያጠቃ ከሆነ በዱር አንሰሳትስ ይህንን አይነት ሁኔታ አይደለም ወይ የምናዬው? ብዙ የቆሰሉ ሰዎችን አየሁ አብዛኞቹ እጅና እግራቸውን አጥተዋል፡፡ እነዚህ ሰዎች የተገኘባቸው ወንጀል ቢኖር አባት አገራቸውን ለመከላከል መሞከራቸው ብቻ ነው፡፡ ታዲያ ይህ በራሱ ድል አደረግን ተብሎ ሲጨፈር አንድ ጠብታ ቅሬታ ወይም ቁሰል መፍጠር አልነበረበትም ወይ?

በመጣሁ በሁለተኛው ቀን የፊታውራሪ ነጋሽ ልጅ ሞተ፡፡ ሽማግሌው ስሜታቸውን በምንም መንገድ አላሳዩም፡፡ እንደገናም ጀግና ሰው መሆናቸውን አስመሰከሩ፡፡

"ደህና ሁን ልጄ፡፡ አሁኑኑ እኔው እከተልሃለሁ" ነበረ ቃላቸው ያረፈውን የልጃቸውን ቅንድብ እየሳሙ፡፡ እኔም በዚህ አምልኮና ህሲናን በሚፈትሽ ሰአት ተካፋይ ነበርኩ፡፡



*የደጃዝማች አያሌው ተወካይና የሥንቅና ትጥቅ ሀላፊ የነበሩት ፊታውራሪ ተሻገር*

*በቤተሰቦቻቸው መልካም ፈቃድ*



# ምዕራፍ አሥራ ሶስት

## የአፍ ጋጋ ጦርነት

በእንዳባጉና በተደረገው ድርጊት ጠላት በንዴት የተቃጠለ ይመስላል፡፡ ከጠዋት እስከ ማታ ትልልቅ ባለ ሶስት ሞተር ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች ራስ እምሩና ደጃች አያሌው ያሉበት ካምፕ ላይ ሲያንዣብቡ ይውላሉ፡፡ ትልቅና ትንንሽ ቦምቦች የተገኘው ቦታ ላይ ሁሉ ይጣሉ ነበር፤ እኛም ከፍንዳታው ድምፅ ጋር ተላምደናል፡፡ ጉዳቱ መጠነኛ ነው የነበረው ምክንያቱም ጦሩ በሀያ ኪሎሜትር ካሬ ስፋት በየቦታው ተሠራጭቶ በየዋሻውና በየጉድጓዱ ተደብቆ ስለነበር ነው፡፡




*የሰማይ ላይ "ጭራቆቹ" የጣሊያን ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች በቡድን ሲበሩ*

በገበሬው ቤት ያሳለፍኳቸው ቀናቶች በሙሉ ነርቭ የሚሰቀጥጡ ነበሩ፡፡ ከረዥም ጊዜ በኋላ እሁን ረጋ ባለ መንፈስ ሆኜ ሳስበው እንዴት አድርገን እንደዚያ ያለ አእምሮ የሚበጠብጥን ነገር እንደተቋቋምነው ሊገባኝ አይችልም፡፡ ቦምቦች ቀረብ ባለ ቦታ ሲፈነዱ ወዳዘጋጀሁት መጠለያ

እየተንፏቀቅሁ እገባለሁ:: መጠለያዬም በዕቃዎች በፍራሽና በኮርቻ መሀከል ነበር:: በዚህ መንገድ ትንሽ ደህንነት ይሰማኝ ነበር::

የድሬሰሩ የፈጠነ ነገር ግን የባሰ ነበር:: ደብረ አባይ እያለ ቦምብ ሲወርድ ስላየ አውሮፕላን በጮኸ ቁጥር እርፎ መቀመጥ አይችልም ነበር:: ላያስበው አየሮጠ አውሮፕላኑ ወዴት እንደሚሄድ ለማየት ይወጣና "ዶክተር እየመጣች ነው" "she is coming" ይላል:: ፈጠን ሲፈራ በእንግሊዝኛ መናገር ነው የሚቀናው:: ደግሞ እየሮጠ ተመልሶ ይገባል:: እኔም ድምፁን እጥፍቶ መጠለያው ውስጥ እጠገቤ እንዲጋደም ትዛዝ እሰጠዋለሁ:: እንደ ውሻ ነው የሚታዘዘው:: ነገር ግን ወዲያው ተነስቶ ደግሞ መልሶ ይወጣል:: እሱን እርፎ እንዲቀመጥና ዝም እንዲል ማድረግ አይቻልም::

በእንግሊዝኛ "ዶክተር እናታችን ላይ ናት:: ርግጠኛ ነኝ የመጨረሻችን ቀን ነው! ምን ማድረግ ይሻለናል?" ማበረታታት ሆነ መገሠፅ ወይም መቅጣት ሊያቆመው የሚችል ነገር አይደለም:: ተሰፋ ቢስ! የሚያደርገውን እንዲቀጥል መተው ይበጃል!

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እንደተጋደምኩ በሳቅ እንፈራፈራለሁ:: የሚያደርገውን ነገር ማየት የሚያስቅ ነበር፤ ግማሽ ሰውነቱን ከበሩ ውጭ እድርጎ የአውሮፕላኖቹን እንቅስቃሴ ለመመልከት አንገቱን ግን ወደ በሩ ወደኋላ አጣሞ መሬት ላይ ይተኛል::

እኔም ብሆን በጣም ሲበዛብኝ አንዳንድ ጊዜ እየዳህኩ ወደ ሜዳው ወጥቼ በረዥም ሳሮች ውስጥ እደበቃለሁ:: ፈጠንና ሌሎች ድሬሰሮችም እኔን ተከትለው ይወጣሉ:: ንፁህ የሚነፍሰው አየርና የፀሀይዋ ሙቀት አእምሮየን ያረጋጋዋል:: ድንገት ጎጆው ቢመታ ደግሞ ጎጆው ውስጥ እንዳለን አለመቀበሩም ሌላ ማረጋጊያ ጭምር ነው::

አውሮፕላኖቹ ሲሄዱ ተመልሰን ጤነኛ ሰዎች እንመስላለን ግን እስከሚቀጥለው ጊዜ ድረስ ነው::

ሌሎች ጉዳዮችና ሥራ ጊዜያችን ስለሚወስዱልን ሳቅና ጨዋታችን እንደተጠበቀ እንዲቆይ አድርገውልናል:: ከመጠን በላይ የሆኑ ንብረቶችና ሌሎችም እቃዎች በእንዳባጉና ጦርነት ተገኝተዋል:: የተለያዩ አይነት ዕቃዎች በየዋሻው ውስጥ ተደርድረዋል:: የፍራፍሬ ጭማቂ ጠርሙሶች፣ ዶቄት፣ ስኳር፣ የሬድዮ ክፍሎች፣ መድሃኒቶች፣ ወይን በጠርሙስ፣ ዘይት፣ ቅቤ፣ መላረያዎች፣ ጥጥ፣ የተጠበሰ ዳቦ በሣጥን፣ የአልጋ ልብስ፣ የስፓኒሽ ከፍያዎች፣ አልጋ፣ ጋዜጣ፣ ብሎኖች፣ ልብሶች፣ መፅሀፍቶች በየዋሻው ተከምረዋል::



በተጨማሪም ሁለት አዲስ ግራማፎኖች፣ ሶስት ታይፕ መፃፊያዎች እና ስላላ የፎቶ ካሜራዎችም ነበሩ::

ወታደሮች በመጀመሪያ ማወቅ የፈለጉት ነገር ምግቦቹ መርዝነት እላቸው ወይም መበላት የሚችሉ መሆኑን ነው:: እኔ እንድቀምሳላቸውና እንዳረጋግጥላቸው ይፈልጋሉ፤ ከቀመስኩ ደግሞ ከምግቡ ባለንብረት ፊት መሆን አለበት::

ወዲያውኑ ላረጋግጥላቸው አቻል ነበር ምክንያቱም ጣልያኖቹ እስከመጨረሻው ሰአት ድረስ ምግቦቹን ይጠቀሙ እንደነበርና ሲለቁም በችኮላ ለቀው ስለወጡ ነው:: ለማንኛውም ግን ለማረጋገጥ ብለን እንዱን አህያ ከዱቄቱ፣ ከሰኳሩና ከተጠበሰው ዳቦ እንዲበላ አደርግን::

አህያውም ምንም አልሆነም ወታደሮችም ተረጋጉ

ከታሸጉት ምግቦች መሀል ወታደሮች የፈለጉት ሳርዲኑን ብቻ ይመስላል:: ሌሎቹን ለምሳሌ ሳልመን (የአሳ ዝርያ)፣ ስጋ፣ የተለያዩ ፍራፍሬዎች፣ ሎብስተር፣ ማርማላት የመሳሰሉትን ለድካሜ ዋጋ የምቸለውን ያህል መውሰድ ቻልኩኝ:: የቀረው ወደ እንድ ሺ የሚሆን ጣላ ለሽያጭ እንዲቀመጥ ሆነ::

እነዚህ ነገሮች ዋጋቸው ምን ያህል እንደሆነ ስለማያውቁ ወደ ሀኪሙ እየመጡ ዋጋቸውን እንድነግራቸው ይጠይቁ ነበር:: አሁን መሸጥ መግዛትና እርስ በራሳቸው መነገድ ጀምረዋል:: እዚህ በታም ቢሆን ሌላ ቦታ እንደሚደረገው ሁሉ የዕቃ ዋጋ እንደተፈላጊነቱና እንደዕጥረቱ ነው::

አንዳንድ በጣም የሚፈለጉ እቃዎች በመጠኑ ነው የተገኙት:: በተቃራኒው ደግሞ የማይፈለጉ ዕቃዎች በብዛት ይገኛሉ:: በፍፁም አዲስ የሆነ ግራማፎን (ማስተርስ ቮይስ የሚባል ስም ያለው) ከስስት ሸክላዎች ጋራ ዋጋውን በአራት ማርትሬዛ ተመንኩት:: ታይፕ መፃፊያዎች ያን የህል ጥቅምም አልነበራቸውም:: ትልቅ ታይፕ መፃፊያ በሶስት ማርትሬዛ ገዛሁ:: የኋላ ኋላ የዋጋዎችን ዝርዝር በፅሁፍ አዘጋጀሁ፤ እስዚያ እረፍት አላገኝም::

አንድ ቀን አንድ ወታደር ወረቀቶች በጁ ይዞ መጣና የምገዛው ከሆነ ጠየቀኝ::

አዎ በርግጥ ዋጋውን ከፍ ካላደረገ በስተቀር አገዛለሁ::

ሰውየው ለለምንት አንድ ሺ የጣልያን ሊሬ ኖቶች ሃምሳ ማርትሬዛ ጠየቀ:: ከሌሎች ከተዘረፉ ንብረቶች ጋራ የጠላት ካዝና ተገኝቷል፤ በውስጡም ብዛት ያለው የጣልያን ሊሬ ተገኝቶበታል::

እነዚህን በደንብ የተሣሉና የተዘጋጁ ወረቀቶች እውነተኛ ዋጋቸውን እስኪያውቁ ድረስ ብዙ ቀን ወለደባቸው:: በመጀመሪያ ዝም ብለው በየሜዳው እየጣሉ ለነፋስ ይበቱናቸውም ነበር:: በኋላ ግን ትግራይ ውስጥ ባለንበት ጊዜ በሙሉ በነዚህ ወረቀቶች ሞቅ ያለ መገበያየት ነበረ:: በኔ ግምት ወደ ግማሽ ሚሊዮን የሚሆን ሊሬ በዚሁ ገበያ ሲዘዋወር ነበር::

ወታደሮችም በጦርነቱ ለዘረፉት ወይም ለያዙት ነገር በሙሉ እንዲከፈላቸው ፈለጉ ለመድሃኒቶች፤ ለቁስል መጠቅለያ ጨርቆች፤ መሳሪያዎች ጭምር:: ስለዚህ ደጃች አያሌው ገንዘብ እንዲሰጡኝ ጠየቅሁኝ:: እሳቸውም ሁለት መቶ ማርትሬዛ ላኩልኝና ለአገኘኋቸው ዕቃዎች መግዣ ተከፋፈለ:: የነበረኝ የመድሃኒትና መሳሪያዎች መጠን ሲጨምር ሳይ ደስታዬ ከልክ ያለፈ ነበር:: እሁን ያለኝ የመድሃኒትና መሳሪያ መጠን ለወራት ያህል እንደሚያዳርሰኝ ነው፤ ነገር ግን ሁሉም እልነበርም ምክንያቱም ኤተር(ለማደንዘዣ የሚሰጥ) የሚባል መድሃኒት አንዲ ኪሎ ብቻ ነው የነበረኝ:: እራሴን ደግሞ የዚህ መድሃኒት ዕጥረት ቢኖርም በቁለል አካባቢ በሚሰጥ ማደንዘዣ እጠቀማለሁ ብዬ እረጋጋሁኝ:: እቢሲኒያኖች ደግሞ ህመም የመቋቋም ችሎታ ስላላቸው ለቀላል ቀዶ ህክምና ሥራ ማደንዘዣ አይፈልጉም ነበር::



ማርተሬዛ (ማርያ ቴሬዛ) በዚያን ጊዜ መገበያያ ገንዘብ በፊት ለፊትና ጀርባ

ደጃች አያሌው ገንዘቡን ሲልኩልኝ ጣልያኖቹ መሀል አገሩን በቦምብ መደብደብ እንደጀመሩ እስታውቀውኛል:: የደብረ አባይ ገዳም ከነሚያምረው ቤተክርስቲያኑ አመድ ሆኗል:: በየሁለቱ ቀን ዳባት በአየር ይደበደብ ነበር:: እሁን እርሻውን ሰፈሩንና መንገዶችን በቦምብ ይደበድቡ ጀመር:: በፀለምት አንድ ትንሽ ልጅ ያልፈነዳ በምብ አግኝቶ ጓደኞቹን ጠርቶ

"ይሀ እሰቀያሚ ነገር ነው እባቶቻችን የሚገድል ኑ እንደብደበው"



በማለት ባለማወቃቸው በንዴት በድንጋይ እስኪፈነዳ ድረስ ደበደቡት:: እንግዲህ እነዚህ ንፁህ ትንንሽ ፍጥረቶችም የወራሪው መጥፎ መሳሪያ ሰለባ ሆነዋል::

በተጨማሪ ደግሞ ሶስት ፊታውራሪዎች ማለትም ተሻገር፤ ገሰሰ እና ሽማግሌው ሳይሆኑ ነጋሽ ከበለሳ ወደ ግንባር ጦር ወደ እፍ ጋጋ እንዲሄዱ መታዘዛቸውን ሰማሁ::

አፍ ጋጋ ወደ አክሱም ወደሚሰደው መንገድ ማለፊያ በር ነው:: የሚገኘውም በተከዜና በእንዳለላሴ የጠላት ምሽግ መሀከል ባለ ቦታ ነው:: እንግዲህ ጣሊያኖቹ ጥቃት ቢጀምሩ የመጀመሪያውን ጥቃት ሊቀበሉ ነው:: የፈለገው እመቺ ሁኔታና አጋጣሚ ቢፈጠርም ምንም እይነት ጥቃት እንዳይሰነዝሩ ተከልክለዋል::

ራስ እምሩና ደጃዝማች ለለወታደሮቻቸው እቀማመጥ የተለማሙ መሆናቸውንም ሰማሁ:: የራስ እምሩ ሰዎች ወደ አክሱም በሚወሰደው መንገድ በምእራብ በኩል እንዲቆዩ፤ የደጃች አያሌው ሰዎች ደግሞ በምሥራቅ በኩል እንዲሆኑ ሆኗል:: በዚህ መንገድ ጥላቻ ስሜት እንዳይፈጠርና በሁለቱ ሡራዊት በኩል የማይሆን ከርከር እንዳይጀመር ነው::

አንድ ቀን ፀሀይ ሳትወጣ በሽተኞች እይቼ ወደቤቴ ሰመለስ ሶስት የጣልያን ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች ድንገት እየሁ:: የገረመኝ ነገር ደግሞ ከእንደኛው አውሮፕላን ትልቅ ነገር ወደመሬት ሲጣል ቀስተደመና በመሰለ ህብረ ቀለም ተከትሎ በሚያፏጭ ድምፅ መሬት ላይ ወደቀ:: ወዲያውኑ ለምተነው የማናውቀው እይነት የፍንዳታ ድምፅ ሶስት ጊዜ ሰማን:: ሌሎቹ ሁለቱም እውሮፕላኖች ተመሳሳይ ቦምብ ጣሉ::

እኔ እንዳየሁት ሁሉ ድሬሰሮቹም እይተዋል:: እኔም ይህ አዲስ ነገር ምን ይሆን ብየ እሰብኩ፤ የራሴ ጥርጣሬ ነበረኝ ግን እርግጠኛ አልነበርኩም::

ልክ እውሮፕላኖቹ እንደሄዱ ቦምቡ ወደ ተጣለበት እቅጣጫ ሮጥን:: የወደቀው ከኛ ቦታ ሶስት መቶ ሜትር ርቆ ከሚገኝ ትልቅ የእርሻ ቦታ ነው:: ልክ ከቦታው ለመድረስ ሲሰ መንገድ ሲቀረኝ ድንገት እንግዳ የሆነ የነጭ

ሽንኩርት ወይም መስታርድ ሽታ ሸተተኝ፡፡ የትኛው እንደሆነ መለየት አልችልም፡፡ ለማንኛውም ግምቴ ልክ ነበር፡፡ የጋዝ ቦምቦች ነበሩ፡፡

"መርዝ! መርዝ!" እያሉ ሰዎች እየጮሁ ከሜዳው እየሮጡ ይወጡ ጀመር፡፡

እኔም ዞሬ መሮጥ ጀመርኩ፡፡ የነበረኝ የመርዝ ጋዝ መከለያ ጭምብል ቤቴ ውስጥ ግድግዳው ላይ እንደተንጠለጠለ ነበር፡፡

አንድ የጋዝ ቦምብ ብቻ ነው መሀል እርሻው ላይ የወደቀው፡፡ ሌሎች ሁለቱ ራቅ ብሎ ሜዳው ላይ ከእርሻው ማዶ ነው የወደቁት፡፡ በውጤቱ ሰባት ሰዎች ሲሞቱ ዘጠኙ ቆስለዋል፡፡ ሁሉም የሞቱት የቤት አገልጋዮች ነበሩ፡፡ አንድ ቤት ውስጥ ሆነው እህል እየፈጩ ዳቦ ይጋግሩ ነበር፡፡ የመርዝ ጭሱ በከፍቱ በር በኩል በበቂ መጠን ገብቶ ሳንባቸውን በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ አቃጥሎታል፡፡

ከቆሰሉት መሀል ደግሞ ሁለቱ አይነ ስውር ሆነዋል፡፡ አንዱ ገና የአሥራ አራት አመት ልጅ ነበር፡፡ በፍንጣሪውና በመርዝ ጋዙ ብትከትክ ብሎ ቆስሎ ስለነበር ከሳምንት በኋላ  ሞተ፡፡ የቀሩት የቆሰሉት ስድስቱ ቆይተው አገግመዋል፡፡

ማስታወሻ መያዣ ካላንደሬ ጠፍቶብኝ ሊቀር ነበር ነገር ግን ከዚህ ድርጊት ከሁለት ቀን በኋላ  አገኘሁት፡፡ ቀኑን ሳየው የመርዙ ቦምብ የጣልያኖች የገና ስጦታ ነበር፡፡ ቦምቦችን የጣሉት የገና ዋዜማው እለት ነው፡፡ እኔም ትልቁ በአላችን መምጣቱ ትዝም አላለኝም ነበር፡፡ የሃበሾች ገና ከአውሮፓውያን ገና አሥራ አራት ቀን ዘግይቶ ስለሚከበር እኔም አብሬ በዛው ቀን ባከብር ይሻለኛል ብዬ ወሰንኩ፡፡

በአውሮፓውያን ገና የቀኑ ለት ጠዋቱኑ ከፊታውራሪ ተሻገር የተላከ ደብዳቤ ደረሰኝ፡፡ የጣልያን ሬጅመንት እከሱምን ለቆ ወደ አፍ ጋጋ እየሄደ ነው፡፡ ውጊያ የማይቀር ነገር ነው ስለዚህ ሁለት ድሬሰሮች ከመሳሪያና ቁስል ማከሚያ ቁሳቁስ ጋራ በአስቸኳይ እንድልክ ጠየቁኝ፡፡ እኔም ወዲያውኑ ሁለት በቅሎ ጭነት ሙሉ ጓዝ አዘጋጀሁኝ፡፡ ነገር ግን መንገድ ወዲያውኑ መጀመር አልቻልንም፡፡ ምክንያቱም ሁለት አውሮፕላኖች በኛና በእንዳ ስላሴ መሀል ባለው ሜዳ ላይ እያንዣበቡ ነበር፡፡ ተደራቢ ወይም ተጨማሪ ሀይል እንዳይሻገር እየከለከሉ እንደነበር ግልፅ ነበር፡፡ ሆኖም ከአፍ ጋጋ በኩል ምንም አይነት የተኩስ ድምፅ ገና አልሰማንም፡፡ እያቅማሙ ሁለቱ ድሬሰሮች አውሮፕላኖቹ ከሄዱ ከአንድ ሰአት በኋላ ሄዱ



ይህ ሁሉ ሲሆን ሽማግሌው ፊታውራሪ ነጋሽ የተረፉቸውን ጦር አሰባስበው ድንገት የሚፈስጉ ከሆነ በማለት የዘንባባ ዛፎች ጫካ ውስጥ ሆነው ይጠባበቃሉ፡፡ የወታደሮች የውጊያ ፍላጎት ምንም አልቀነሰም ከምንም ጊዜ በላይ ያቅራሩና ይፎክሩ ነበር፡፡

ከቀኑ ሰባት ሰአት የተኩስ ድምፅ ይሰማ ጀመር፡፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ተከታታይ የተኩስ ድምፅ መሰማት ቀጠለ፡፡ ውጊያው በሙሉ ሀይል እየተካሄደ ነው፡፡

በሩቅ መነፀር ስመለከት የኛ ሰዎች በድንጋዮችና በዛፎች ጀርባ አድፍጠዋል፡፡ ነገር ግን ሲተኩሱ ጉፍ እያለ ወደ ሰማይ የሚወጣውን ጭስ ሳይ በሚያሳዝን ሁኔታ አብዛኛው ጦር የያዘው መሳሪያ ያለፈበት አሮጌ ሞዴል መሆኑ ትዝ አለኝ፡፡ እንዲያውም በጭሱ ምክንያት የጠላት ኢላማ እንዲሆኑ ነው ያደረጋቸው፡፡

አልፎ አልፎ ወታደሮች በቡድን እየዘለሉ ወደፊት ሲሮጡ ይታያል፤ ወይም የተስማሙዱትን የከበባ ዘዴ ይሞክራሉ ሆኖም በየጊዜው ወደኋላ እንዲያፈገፍጉ ይገደዳሉ፡፡ ጠላትን ማየት አልቻልኩም ምክንያቱም ቆየሳ ጋራ ጀርባ ተከልለው ነበር፡፡

ብዙ ሰአታት አለፉ፡፡ ከፊታውራሪ ተሻገር የተላከ ትንፋሽ የሚያጥረው ሰው እየሮጠ መጣ፤ የተላኩት ድሬሰሮች አልደረሱም ብሎ ነገረኝ፡፡ መልከተኛውም ድሬሰሮቹን ከወንዙ ባሻገር ከሜዳው ሳይደርሱ ዛፍ ስር ተቀምጠው ያያቸው መሆኑን ጠቆመኝ፡፡ የተረገሙ ፈሪዎች ህይወታቸውን ለማዳን ሀላፊነታቸውን ዘንግተዋል፡፡

አስር ሰዎች ያሉበት አጃቢ ከፊታውራሪ ነጋሽ መጣልንና መንገድ ጀመርን፡፡ ብዙ ኪሎሜትሮች ተጉዘን ከወንዙ ማዶ እንደደረስን አስፈሪ የሆነ የአውሮፕላን ድምፅና ፈንጂ መሰማት ጀመርን፡፡ በደንብ ለማየት ጋራ ላይ ወጣን፡፡

አንድ በአንድ እየተከታተለ የአቧራ  ጭስ ሽቅብ እንደምሰሶ ወደላይ ትጉልል ይልና ወዲያውኑ በየአቅጣጫው ሲፈነጣጠር እናያለን፡፡ ሀያ ሰባት አውሮፕላኖች በዙሪያው እያንዣበቡ በየቦታው ድምሰሳና ጥፋት ያስፋፋሉ፡፡ በተጨማሪ የኛ የቀዳሚው ጦር ስንቅና ትጥቅ ከፍል ሰዎች በሜዳው ሲሮጡ አየሁኝ፤ በአውሮፕላኖቹ ጥቃት እየደረሰባቸው ነበር፡፡ ውጊያው ጨበጣ ስለነበር  የራሳቸውን ሰዎች ላለመጉዳት አብራሪዎቹ ውጊያው ቦታው ላይ ቦምብ መጣል አልደፈሩም፡፡

በዚህ ሁኔታ ውጊያው ወዳለበት ቦታ መቀጠል አልተቻለም። ከዛፉ ስር ያገኘኋቸው ድሬሰሮች ለራሳቸው መጠለያ እንዲፈልጉና ጓዙንም እንዲጠብቁ ትዛዝ ተሠጣቸው። እኔና አጃቢዎቼ ባየነው ነገር ፈዘን ጋራው ላይ ባሉ ቁጥቋጦች ስር ቆምን።

እሁን ወደ ማለፊያው በር በመሄድ ቦታ እየያዘ ያለውን የጠላት ጦር ማየት ቻልን። አቢሲኒያኖች ደግሞ በእልከ መቋቋም ጀመሩ። አንድ ቡድን ጣልያኖችን ከጀርባ ለማጥቃት ወደ ቆየትሳ ተራራ ሲገሰግስ በብዙ የጣልያን አውሮፕላኖች ታየ ያም ሆኖ ተበታተኖ ግፊቱን ቀጠለ።

አቢሲኒያኖቹ መሪ እንደነደላቸው ማየት እችላለሁ በጭራሽ መሪ ያለም አይመስልም። በመቶ በመቶ ሰዎች ያሉባቸው ቡድኖች በየአቅጣጫው ይተራመሳሉ፤ ብዙ ጊዜም እርስ በራሳቸው ይተላለፉ ነበር።

በሌላ በኩል ጣልያኖቹ ያለማቋረጥ ወደፊት ይገፉሉ። ተፋላሚዎቻቸው ኢትዮጵያውያኑ ጣልያኖቹን ከጀርባ ለመከበብና ለማጥቃት መንገዱን ከፍተውላቸው የሄዱ ይመስላል። ይህ ታክቲክ ጠላትን ያሳሰበው ይመስላል። ነገር ግን የኛ ሰዎች ለረዥም ጊዜ ውጊያውን መቀጠል ይችላሉ ወይ?

"እሀ! ተመልከት! ያ ምንድን ነው?"

እውሮፕላን በላያችን ላይ አለፈና ቁልቁል ወርዶ ከኛ የኪሎ ሜትር ርቀት ላይ አረፈ። ገና ሞተሩ ሳያቆም ሶስት ሰዎች ዘለው ወጡና ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ መሮጥ ጀመሩ።

ወዲያውኑ ሌላ እውሮፕላን በላያቸው ላይ ከነፈ። ነገር ግን በራሱ እንደ እንዝርት መሽከርከር ጀመረና በአፍንጫው ተከሰከሰና ተገልብጦ በጀርባው እንደወደቀ በእሳት መያያዝ ጀመረ። ይህ ሁሉ በጥቂት ሰከንዶች ውስጥ ነው የሆነው። ገና ምንም ቃል ሳልተነፍስ የኔ አጃቢዎች የሚሮጡትን ጣልያኖች ለመያዝ ወደ ሜዳው መሮጥ ጀምረዋል። እነሱን ያዩ ሌሎች ደግሞ ተከተሏቸው። የጣልያን እውሮፕላኖች አሳዳጆችን ለመግታት በመሞከር አውቶማቲክ መሳሪያ በቅርብ ተጠግተው ይተኩሱና ቦምብ ይጥሉም ነበር። በማለፊያው በር ያለው የጣልያን አዛዥ ሶስቱ ጓዶቹ ያሉበትን አደጋ ይመለከት ነበር።

ከዚህ ቀጥሎ አይቸው የማላውቀው አስደናቂ ትዕይንት ተፈጠረ። ወደ መቶ የሚሆኑ ፈረሰ ጋላቢዎች ከማለፊያው በር በኩል የአቧራ ጉም እያስነሱ መጋሰብ ጀመሩ(ቁጥራቸውን ወደኋላ ነው ያገኘሁት)። እንገታቸውን ወደ ፊት



ለግደድ አድርገው ሲከንፉ ፈረሶቹ መሬት ላይ የተኙ ነው የሚመስሉት። ጋላቢዎቹ ደግሞ ወይ የፈረሶች አንገት ላይ ተጋድመዋል፤ ወይም ፈረሱ ላይ ቆመው ወይ ወደኋላ ዞረው ተቀምጠው በግራና በቀኝ እየተኮሱ የጦርነት ጩኸት ያሰማሉ። ሌሎች ሳይሆኑ ካዛኮች ወይም የሰሜኝ አፍሪካ አረቦች ናቸው እንዲህ አይነት ግልቢያ የሚችሉት ብዬ አሰብኩ። ከትሪፖሊ (ሊቢያ) የመጡ ስፓሂዎች(ፈረሰኞች) ነበሩ።




(ስፓሂ ዲ ሊቢያ በሮማ ትርኢት በማሳየት ላይ እያሉ የተነሳ ፎቶግራፍ እኤአ 1936. Sebastian O'kelly, Amedeo: A True Story of Love and War in Abyssinia) በስባስቲያን ኦኬሊ መልካም ፈቃድ

ሶስቱ የሚሸሹት ጣልያኖች ጋላቢዎቹን ሲያዩ ወደነሱ ሮጡ ወዲያውኑ ፈረሰኞቹን ተቀላቅለው ተሰወሩ። ጋላቢዎቹ ፍጥነታቸውን የቀነሱ በሚስልም ያቆመ ሰውም አልነበረም። ከዛም ትልቅ ከብ ሰሩና በመጡበት ፍጥነት ወደ አቢሲኒያኖች ተመለሱ። ትከ በማይገኝለት ድፍረት ሞትን ሳይፈሩ በመደናገጥ ከፈዘዙት አቢሲኒያኖቹ መሀከል ገብተው ማጥቃት ቀጠሉ። ማቆሚያ የሌለው ከሚመስል አንድ ሰአት በኋላ ጋላቢዎቹ ወደ ማለፊያው በር ተመለሱ።

---

*እነዚህ ፈረሰኞች በደንብ ከሚታወቁት የፈረንሣይ ስፓሂዎች የተለዩ ናቸው። ለዚህ ነው ስፓሂ ደ ሊቢያ ተብለው የሚጠሩት። ኢጣልያኖች ኢትዮጵያን በወረሩበት ጊዜ ይህን የሊቢያ የፈረሠኛ ቡደን መጠቀማቸው ተዘግቧል። ጣልያኖች በአፍሪቃ ከነበሯቸው ቅኝ ግዛቶች አንዱ ሊቢያ ነበር።*

ጣልያኖቹን አድነዋቸዋል ግን አምስት አረቦችና ፈረሶች ሜዳው ላይ እንደተጋደሙ ቀርተዋል፡፡ የአረቦቹ ጋላቢዎች ላይ የነበረውን ትኩረት ለመቀነስ ቃኘ የአሰካሪስ ወታደር ቡድን በሜዳው በግራ በኩል ሄዷል፡፡ ነገር ግን በሁሉም አቅጣጫ ተከበ ነበር፡፡ ሌላ ተጨማሪ ቡድን ደርሶ ባያስጥላቸው ሙሉ በሙሉ ይደመሰሱ ነበር፡፡




*በሰባሰቲያን ኦኬሊ (Sebastian O'Kelly) መልካም ፈቃድ*

*አሜዲዮ የተባለ የጣልያን መኮንን ከአጃቢ ስፓሂው ጋር በፈረንጆች በገና ማግስት የተነሳው ፎቶግራፍ፡፡ ይህ ሠው ከሊቢያ ሁለት ሺ የሚሆኑ እነዚህን ፈረሰኞች ይዞ ወደ ኢትዮጵያ መምጣቱ በመፅሐፉ ተዘግቧል፡፡ መኮንኑ በሰለህለህ አፋ ላይ እንደቆሰለም ተዘግቧል፡፡ በዚህ ውጊያ ኢትዮጵያዊ ተዋጊ ሰውየውን ከፈረሱ ላይ አውርዶ ለመግል ያደረገው ሙከራ አልተሳካለትም፡፡ መኮንኑ ለኢትዮጵያውን ተዋጊዎች አክብሮት እንዳለው አሜዲዮን በቅርብ ከሚያውቀው ከመፅሀፉ (Amedeo: A True story of Love and War In Abysisinia) ደራሲ (Sebastian O'Kelly) ጋራ ባደረግነው ልውውጥ መረዳት ችለናል፡፡*



ከባድ ውጊያ ቀጠሰ፡፡ ብዙ የጣልያን መኮንኖች ሞቱ፤ የጠላት ጦርም ተበታትኖ ወደኋላ ማፈግፈግ ጀመረ፡፡በዚህ ሰአት ከተራረው ጆርባ የሄደው የአቢሲኒያኖች ጦር ከጆርባ ያጠቃ ይመስላል ምክንያቱም ጨለማው ሳይመጣ ጣልያኖቹ ማሰፊያ በሩን ትተው ሸሽተዋል፡፡ ከዚያ ከግማሽ ሰአት በፊት የመጨረሻው አውሮፕላን ተመልሶ ሄዷል፡፡




የስፓሂ ዲ ሊቢያ ፈረሰኞች የጣልያን እግረኛ ጦርን እየመሩ
(በሲባሰቲያን ኦኬሊ (Sebastian O'Kelly) መልካም ፈቃድ)

አቢሲኒያኖች ማታውኑ በዚያው ቦታ አደሩ

የውጊያውን የተለያየ ደረጃ ሰከታትል ተመስጬ ሰለነበር ሰለራሴ ምንም ሳላስብ ብቻዬን መቅረቴን አላሰተዋልኩም ነበር፡፡ አጃቢዎቼ አልተመሰሱም ድሬሰሮቹም የት እንደሄዱ አላወቅሁም፡፡ ወደ ቦታዬ ብቻዬን መንገድ መጀመሩ ራሰን ከመግደል ነው የሚቆጠረው በዚህ ግርግር ሰአት ብቻውን የሚጓዝ ነጭ ሰው ከታየ ሰመተኮሰም የሚያቅማማ አይኖርም፡፡

ያለሁበት ቦታ ሌሊቱን ማሳለፍ ነበረብኝ፡፡ ሲነጋ ሰው እኔን ፍለጋ መምጣቱ አይቀርም፡፡ በቅጠሎቹና በቅርንጫፎች መኻታ አዘጋጆቼ ወዲያውኑ ተጋደምኩ፡፡ እሳት ሰማንደድ አልደፈርኩም፡፡ እንቅልፌ አልመጣም ነገር ግን አልተሰላቸሁም ነበር፡፡

ሀሳቤ ቀን በሆነው ነገር ላይ ነበር በተለይ ከጣልያኖቹ በኩል ፈረሰኞቹ ተአምረኛ በሆነ መንገድ ጣልያኖቹን ያዳኑበት ሁኔታ፡፡ እኔ እንኳን ፈረስ የምወድ ሰው አይደለሁም፡፡

ከጥዋቱ ሶስት ሰአት ሲሆን የሆነ ሰው "ሀኪም" ብሎ ሲጣራ ሰማሁ፡፡ የተከበሩት ሽማግሌ ፊታውራሪ ነጋሽ ራሳቸው ነበሩ፡፡ እንደሳቸው አባባል ከሞት ሊያድኑኝ ነው የመጡት፡፡ በውጊያው ሳቢያ ሁሉም ሰው ረስቶኛል፡፡

አውሮፕላኖች በጊዜ መጥተው በጦርነቱ ሰምን እንዳልተካፈሉ ማሰብ ጀመርን፡፡ ከቀኑ ዘጠኝ ሰአት እስከሚሆን አልመጡም፡፡ ከብዙ ቀናት በኋላ ሰላዮቻችን ሲመለሱ ምክንያቱ ግልፅ ሆነልን፡፡ እኔም ከጦርነቱ በኋላ ሁለት የኢጣልያ መኮንኖችን አነጋግሬ ሁኔታውን አረጋግጫለሁ፡፡ የገና ለት ጠዋት ሰባት ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች ሙሉ ቦምብ እንደጫኑ ከአከሱም ወደ አፍጋጋ እንዲበሩ ታዘዋል፡፡ ሲድሰቱ ተጭነው ነበር ሰባተኛውን ለመጫን ዝግጅት በሚደረግበት ጊዜ አንድ ነገር ተፈጠረ፡፡ ሁኔታው በትክክል እንዴት እንደሆን አየታወቅም ነገር ግን የሚባለው አንድ ሰው ቦምብ መሬት ላይ ጥሎ ፍንዳታ ተጀመረ፡፡ ጥቂት ደቂቃዎች ዘግየት ብሎ ሁሉም በቦታው የነበሩት ሰባቱ አውሮፕላኖች ወደ ሰማይ ተነሱ በዚህ ጊዜ ግን ወደፊት ሌላ ጉዳት እንዳያደርሱ በፈንጂው ብትንትን ብሰው ነው፡፡



# ምዕራፍ አሥራ አራት

## ዘንዶ

ጣልያኖቹ በገና ቀን በአፍ ጋጋ በተደረገው ውጊያ መሸነፋቸውን ለማመን አልፈለጉም፡፡ ይሄ ደግሞ የሚያሰገርም አይደለም በተለይም የጣልያኖቹ አዛዥ ጄኔራል ዲ ቦኖ ታሀሳስ ስለ አንዳባጉና ውጊያ በሚገርመው መረጃ አይን ሲታይ ጄኔራሉ ባስተላለፈው መልከት ከሁለት ቀናት ከባድ ውጊያ በኋላ ጠላት እንዲሸሽ ተደርጓል ብሎ ፅፎ ነበር፡፡

በርግጥ ከሆን ጣልያኖቹ በመጥፎ ሁኔታ ነው የተጎዱት፡፡ ለዚህ ደግሞ ምንም ጥርጣሬ የለም፡፡ አለዚያ ለምን የዚያኑ ቀን ወደኋላ ወደ አከሱም ተመለሱ? ከዛ በኋላም ለድፍን ሁለት ወራቶች ከአከሱም ውጭ አልወጡም፡፡ ታክቲካዊ ሽሽት ነው ብሎ መናገርም የውነት አይመስልም፤ ምክንያቱም ሀያ መኮንኖቻቸውና ከመቶ በላይ የሚሆኑ ሰዎቻቸው ሞተዋል፡፡ በተጨማሪ ደግሞ ስድስት መትረየሶች፣ ሀያ ሁለት ቀላል አውቶማቲክ መሳሪያዎች፣ ወደ ሁለት መቶ የሚሆኑ ጠመንጃዎች፣ አሥራ ሁለት ሳጥን ሙሉ ጥይትና ሌሎችም ነገሮች ጥለው ባልሄዱና አቢሲኒያኖቹም ባልዘረፉት ነበር፡፡

በኛ በኩል ደግሞ መቶ አሥራ ስምንት ሰዎች ሲሞቱ ሁለት መቶ ሰዎች ቆሰለዋል፡፡

ጣልያኖቹ ሲሸሹ አቢሲኒያኖቹ አላሰደዷቸውም ነበር ምክንያቱም ወዲያው ጨልሞ ነበር፡፡ በተጨማሪ ግን የነሱ ትጥቅና ስንቅ ጓዝ የሚይዘው ወገን ወደኋላ ይጎትታቸው ስለ ነበር ነው፡፡ አውሮፕላኖቹ በተደጋጋሚ ስንቅና ትጥቁን የሚያጓጉዘውን ክፍል ይደበድቡ ነበር፡፡ ወታደሮችም ይህን አስተውለው ስለነበር በጉዳዩ በጣም ተጨንቀው ነበር፡፡ ምናልባትም ወይ ሚስት ወይ ልጅ አለዚያ ታማኝ አሽከር ቆስሎ ሊሆን ይችላል፡፡ ታዲያ ሰዎቻቸውን ወይም ንብረታቸውን እንይ ቢሉ አሁን ማን ያማቸዋል? ውጊያው እንደሆን አልቋል፡፡

ፊታውራሪ ተሻገርና ፊታውራሪ ገሰሰ ያስ ፊታውራሪ ነጋሽ (የበለሳው) ርዳታ የጠላትን ጥቃት ብቻቸውን ባይጋፈጡ ኖሮ የጣልያኖች ሽንፈት በጣም ግልፅ ይሆን ነበር ። ዕቅዱ ፊታውራሪ ነጋሽ ለእርዳታ እንዲደርሱላቸው ነበረ፤ ግን የራሳቸው የሆነ ችግር አጋጥሟቸው ለሰዎቹ ሳይደርሱላቸው ቀሩ። የሰጡት ምክንያት ቆየሳ ተራራ ያለ ማስፈያን መጠበቅ ነበረባቸው ምክንያቱም ጠላት በዚያ እንዳይመሽግ ለመከላከል ነበር። ነገር ግን ጓደኞቻቸው ምክንያቱን አልተቀበሉትም።

ነጋሽ የበለሳው የጦር አዛዥነታቸውን እንደያዙ እንዲቆዩ ቢደረግም መላው ጦሩ ስለሰውየው ያለው አስተያየት ግን ሌላ ነበር። ከሀዲ ነው ባይባሉም የተረገመ ፈሪ ነው ብሎ ፈርጆባቸዋል። ከዚህ ቀደም ጀግና ነው ተብሎ የሚታወቀው ይህ ሰው በስሙ ላይ የተፈጠረውን ይህን ጥቁር ነጥብ ማስለቀቅ አለበት። ይህ ደግሞ የሚሆነው በጀግንነት ተዋግቶ በማሳየት ነው። በአብዛኛው በራሳቸው ጥያቄ የግንባር ጦር መስርተው አዳጋ ሰኞ በተባለ ከዚህ ቀደም በጠላት ተይዞ በነበረ ቦታ እንዲጠባበቁ ተወሰነ። ቦታው ከአፍ ጋጋ ሰሜን ከአክሱም አስር ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ነው የሚገኘው።

በሚቀጥለው ቀን የአየር ድብደባው የከፋ እንደሚሆን ለኛ ግልፅ ነበር። በዚህ ምክንያት ያለኝ የመድሃኒቶች ጓዝ በሙሉ በሌሲት ሽማግሌው ነጋሽ ወደ እዘጋጁልኝ ትንሽ ዋሻ እንዲወስድ ተደረገ። ያለውን እቃ በሙሉ ፀሀይ ከመውጣቷ በፊት እጓጉዘን ጨርሰናል።

ለራሴ ጥሩ መጠለያ በማግኘቴ ውጭ ምንም አይነት ነገር ቢደረገም በደንብ ማረፍና መተኛት እችላለሁ። ቀኑ ከመጀመሩ በፊት ሁለት ድሬሰሮች አዲስ የቆሰሉ ሰዎችን እንዲረዱ ልኬ ለከትትል ደግሞ ማምሻውን እኔ ራሴ ለመሄድ አቀድኩኝ። በዚያን ጊዜ ቁስለኞቹ የት እንደሆኑም አላውቅም ነበር።

አውሮፕላኖች አልዘገዩም። አምስቱ ከጠዋቱ አንድ ሰአት ሲሆን እየበረሩ መጡ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ጠቅላላ የውጊያ ስፍራውን ቦምብ በቦምብ አደረጉት። ቆስለው የወደቁ የራሳቸውን ሰዎች ለመጨረስ የፈለጉ ይመስላሉ።

ከዚሁ በኋላ ጠቅላላ ሽሬን ያለማቋረጥ እስከሚመሽ ድረስ በቦምብ ደበደቡ። ያን ቀን በላያችን ላይ የወረደውን የብረት ቁራጭ መጠን ማወቅ የሚያጓጓ ነበር።

የአየር ድብደባው ውጤት

የሞቱ፡ ስምንት አሀዮች፤ አንድ በቅሎና ሰስት ላሞች



የቆሰሉ ሁለት ወታደሮችና ሶስት ሴቶች (ሴቶቹ የተመቱት እየሮጡ ወደ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሊገቡ ሲሉ ነው)

ደጃች አያሌው የሞቱና የቆሰሉ ቁጠር ዝርዝር እንዲላክላቸው ጠይቀው ስለነበር እነዚህን ቁጥሮች ትክክለኛ ነበሩ፤ እኔ ራሴ ነበር ያረጋገጥኳቸው።

በፊት እኖርበት የነበረው እርሻ ቦታ ያሉት ጎጆዎች በዚህ ቀን አልተነኩም ነበር ነገር ግን ከሳምንት በኋላ አጠገባቸው የወደቀ ቦምብ ሲፈነዳ ጎጆዎቹ ብትንትን ብለዋል። አጋጣሚ ሆኖ በቦታው ማንም ሰው አልነበረም። በአሥራ ሰባት ምሽት ወደ ሁለተኛው የቁስለኞች ካምፕ ተንቀሳቀስኩ። ቦታው ከቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ቀረብ ብሎ በምሥራቅ አቅጣጫ ኪሎ ሜትሮች ይርቃል። በዚህ ቦታም ያሉት ዋሻዎች በሙሉ ስለተወሰዱ ለራሴ መጠለያ የሚሆን ወደ ገደሉ በኩል ወጣ ካለ አለት ስር ማድረግ ነበረብኝ። ቦታው ከመጠን በላይ ባደጉ የጫካ ፅጌረዳዎች ተሸፍኗል። ማታውኑ በእንጨት በድንጋይና በአፈር አድርገን በጎኑ በኩል ግድግዳ ሠራን።

ለቦምብ መጠለያ የሚሆን አድርገን ሠርተነዋል። ለሥራ ግን በፍፁም የማይመች ሁኔታ ነው ያለበት። የክፍሉ ስፋት ሀያ አራት ካሬ ሜትር ነው። ይህ ደግሞ ለክሊኒክ ሥራ፤ እቃ ማስቀመጫ እና መኝታ ቦታ ሊሆን ነው። ሙሉ በሙሉ ቀጥ ብሎ ለመቆም አይቻልም ምክንያቱም ከወለሉ እስከጣራው ድረስ ያለው ከፍታ አንድ ሜትር ተኩል ብቻ ነው። ነገር ግን ጦርነት ጦርነት ነው እኔም ለራሴ መጠለያ እስካገኘሁ ድረስ ደስተኝ መሆን እንዳለብኝ ተምሬያለሁ። ከውጭ ስማዩን እያየሁ እተኛ ነበር፤ አሁን ግን ያም አይቻልም ምክንያቱም ቅዝቃዜው በዚያን ጊዜ በረዶ መፍጠር ደረጃ ድረስ ይወርድ ነበር።

በአፍ ጋጋ ከቆሰሉት ሰዎች መሀል አብዛኞቹ አግራቸውን ነበር የተመቱት። የሚገርም ነገር ነው ምክንያቱም ሁለቱም ተፋላሚ ወታደሮች ከመቶ ሜትር ርቀት ባልበለጠ ተጠጋግተው ነበር። ስለዚህ በመሀከላቸው በነበረው ርቀት ጥይት ዝቅ ብሎ እግራቸውን ለመምታቱ በቂ ምክንያት አልነበረም። ፊታውራሪ ገሠሠ ሁለት እግራቸውን ተመተው ነበር ቁስሉ ግን ወዲያው ዳነ።

የጣልያኖች ጥይቶች ብዙ ጉዳት የማያደርሱ እንደነበር መቀበል ወይም ማመን አለብኝ። ጣልያኖች የሚይዙት ሞዴል 91 ሌሎች አገሮች ከሚይዙት

መሳሪያ ጋር ሲወዳደር አነስተኛው ካሊበር ነው ያለው ሆኖም ግን ከመጠን በላይ ባሩድ ነበር ያለበት፡፡ እነዚህ ጥይቶች በስጋ ውስጥ እንደመርፌ ሾልከው ሲሄዱ፤ ምንም ስብራት ሳያስከትሉ በአጥንቱ ውስጥ ሰርስረው እንደገናም በደረት ውስጥ ከአንዱ ጎን በሌላው ጎን ከፍተኛ ጉዳት ሳያደርሱ አልፈው ሲሄዱ አይቻለሁ፡፡ ተዋጊ አገሮች የግድ መዋጋት ካለባቸው ሌሎች የሚቃወሙ ሰዎች ማለት የሚፈልጉትን ቢሉም ሌላው ቢቀር አነስተኛ ካሊበር ያላቸው መሳሪያዎች መጠቀም ይችላሉ፡፡ በዚህ ምክንያት የሚቆስሉ ሰዎችና የቁስሉ መጠን ወደ ሚቻለው ዝቅተኛ ቁጥር ሊወርድ ይችላል፡፡

የአቢሲኒያኖችን ህመም መቋቋም ችሎታ ማሳየት በሚችል አንድ ጥሩ ምሳሌ በቀኝ ጆሮው በኩል የቆሰለ አንድ ወታደር አከምኩኝ፡፡ ጥይቱ ከላይኛው አገጭ ስር አልፎ ከጆሮ መግቢያ በኩል ባለ ማስቶይድ በሚባል አጥንት ውስጥ ተቀርቅሯል፡፡ እኔ ማየት የምችለው ነገር ቢኖር የጥይቱን ግማሽ ብቻ ነው፡፡ ጥይቱ በጆሮው ቀዳዳ በኩል ከውስጥ ዘልቋል፡፡

ጥይቱን ለማውጣት ማደንዘዣ መስጠት ነበረብኝ፡፡ ነገር ግን በፍፁም ፈቃደኛ አልነበረም አልፈለገውም፡፡ ከዚያም ማደንዘዣውን በመርፌ ጆሮው አካበቢ ለመጠቀም ፈለግሁ፡፡ እሱም አንዴት እንደሚሰራ ማወቅ መፈለጉን ተናገረ፡፡ እንግዲህ ወደ ጥይቱ ለመድረስ በቢላዋ በጆሮው ቀዳዳ በኩል መቁረጥና ቦታውን ማስፋት ነበረብኝ ነገር ግን ልክ ቢላዋውን ሳነሳ በተቃውሞ

"ቢላዋ አደገኛ ነው" በቀላሉ እንጎሉን ሊወጋው ይችላል አለ፡፡

በጥንቃቄ ነው የሚሰራው ብዬ ቃል ብገባም ምንም አልረዳም፡፡

ስለዚህ በመቀስ በጆሮው ቀዳዳ በኩል ቆርጬ በጥርስ መንቀያ ጉጠት ጥይቱን ማውጣት ቻልኩኝ፡፡ ይህ ሁሉ የሚያሰቃይ ሥራ ሲሰራ፤ በኋላም የተቆረጠው ሰውነት ሲሰፋ ወታደሩ ምንም አይነት የህመም ስሜት አላሳየም፡፡ ልክ አፐሬሽኑ ወይም ቀዶ ህክምናው ሲያበቃ "በጣም ጥሩ ነገር ነው" የሚል ቃል ብቻ ነው የተናገረው፡፡

በዚህ በነበርንበት እ·ዲስ ቦታ በሶስተኛው ቀን ፀሀይ እየሞቅሁ በመርዝ ጋዝ ምክንያት ሲታወር ከደረሰ ወታደር ጋር እያወራሁ ነበር፡፡

"ዶክተር! እባክህ ናልኝ! ሊገለኝ ነው"



ድንገት ፈጠና ከዋሻው ውስጥ ሆኖ ሲጮህ ሰማሁት

ሽጉጤን ውስጥ ትቼው ነው የወጣሁት፡፡ እንደ በሽተኛ የያዘውን ዱላ እየሁና ከእጁ ነጥቄ ወደ ውስጥ ገባሁ፡፡ ወደ ውጭ መውጣት ከሚፈልግ ዘንዶ ጋር ፊት ለፊት ግጥም አልኩ፡፡ እኔን ሲያየኝ ተመልሶ ገባና በግድግዳውና በጣራው ባለ ክፍተት ውስጥ ለመደበቅ ሞከረ፡፡ በሀይለኛ ምት ጀርባውን ግማሽ ወገቡ ላይ መታሁት፡፡

በቅፅበት ዞረና ሰውነቱን ወደላይ ከፍ አድርጎ ወደ ዱላው መጣ፡፡ ጭንቅላቱም ጣራው ድረስ ደርሷል፡፡ አይኖቹ ያበራሉ፤ ምላሱ ከአፉ ውስጥ ብቅ ጥልቅ ይላል፤ በንዴት የሚያሰማውን ድምፅ መስማት እችል ነበር፡፡ በዋሻው ከፍታ ምክንያት ራሴን ዝቅ ማድረግ ስለነበረብኝ ግማሽ ሜትር በማይሞላ ርቀት አይን ለአይን መተያየት ጀመርን፡፡ ዘንዶው ለሕይወቱ እንዳልሳሳ ምንም ጥርጣሬ አልነበረም፡፡ በጅራቱ እግሬ ላይ መጠምጠም ሲጀምር ይታወቀኛል በጣም የፈራሁት ነገር ግን በጭንቅላቱ ራሴን ቢመታኝና ነብሴን ስቼ ብወድቅ ነው፡፡

ይህን ሀሳብ እንደጀመርኩ ወዲያውኑ ኩጉልበቴ ዝቅ በማለት በሀይለኛ ምት ራሱን መታሁት፡፡ ዱላው ከፈለግሁት በታች ዝቅ ብሎ አረፈ ግን እንገቱን ለመስበር በቂ ነበረ፡፡ እንዳለ ሰውነቱ ወለሉ ላይ ዘፍ አለ፡፡ ዋናው ጂምናስቲክ የመጣው ግን ከዚህ በኋላ ነበር፡፡ ተለጣጭ ሰውነቱ እንደ ጅራፍ በዚያች ጠባብ ክፍል ወዲያና ወዲህ ይወናጨፍ ጀመር፡፡ መድሃኒቶቹ በየቦታው ተበተኑ፤ እግሮቼም እንደተጠለፉ ናቸው እና እኔም የሚያሙለጨለጭ ቀዝቃዛ ሰውነት ላይ ወደቅሁኝ፡፡ ቢሆንም በዱላ ድብደባዬን ቀጠልኩ በመጨረሻም ልገድለው ቻልኩኝ፡፡

ይህ ሁሉ ውጊያ ሲካሄድ ፈጠነ ዋሻው ውስጥ የሚችለውን ያህል ርቆ ጥግ ይዞ ቆሞ በፍርሃት የተነሳም ደንዝዞ ነበር፡፡

ሌሎቹ ዱላውንና ትርምሱ ሰምተዋል ያሰቡት ግን በዱላ ፍዳውን የሚያይ ሰው እለ ብለው ነበር፡፡ ቅጣቱን የሚቀምሰው ሰው ማን እንደሆነ ለማየት ወደ ውስጥ መመልከት ጀመሩ፡፡ እኔን ለመርዳት ወደ ውስጥ መግባቱ ግን ትዝም አላላቸውም፡፡ እውነት ነው የኔ የግል ጠባቂ እግሬን ለማስለቀቅ ሞከሮ ነበር ግን በጣምም አልጣረም እንደገናም እልተሳካለትም ዋናው ሃሳብ ዘንዶው ካየለ ለመታገል መዘጋጀት ነበር፡፡

የሀኪሙ ገድል በካምፑ ውስጥ ወዲያው ተሠራጨ፡፡ ሰዎችም ለማየትና እንኳን ደስ ያለህ ለማለት ይጎርፉ ጀመር፡፡ አዛዡ ሳይቀር አንድ ጠርሙስ

ሻምፓኝ ላኩልኝ:: ሻምፓኙን ግን ለሌላ ለበለጠ በአል ብዬ አስቀመጥኩት:: ለመጪው አዲስ አመት ማክበሪያ::

ዘንዶው ሙሉ በሙሉ ያላደገ ገና ወጣት መሆኑ ታወቀ:: ውፍረቱ የከንድ ያህል ሲሆን ርዝመቱ ደግሞ 4.1 ሜትር ነበር:: ከአልጋዬ ስር ተጠቅሎ ተኝቶ ሰንብቶ ነበር:: ሲርበው ነው ከዋሻው ሊወጣ የነበረው::

ታህሣሥ 21 ለኛ በጣም አስቸጋሪ ቀን ነበር:: ለሁለት ሰአታት ሶስት አውሮፕላኖች በካምፓችን ላይ እያንዣበቡ ቦምብ ይጥላሉ:: ዋሻው ውስጥ ተኮራምተን በራሳችን ላይ ፍራሽና ጀንዴ አድርገን ተኝተን ጆሮ የሚበጥሰውን ድምፅ እንሰማለን:: የቦምብ ፍንጣሪዎችና ድንጋዮች ወደ ውስጥ እንደዝናብ እየገቡ ግድግዳውና የመጠለያውን ጎን ይመቱ ነበር:: እንደጉም የሆነው የአቧራው ክምር ለመተንፈስ አስቸጋሪ ሁኔታ ፈጠረ፤ በኋላም ሸፈነን:: ሁሉም ነገር ውፍረት ባለው የአቧራ ሽፋን ተሸፈነ::

በደንገት አንድ ሴት ሰትሮጥ ገባች:: የለበስነውን ገፋ በመሀከላችን ዘላ ገባች:: ሰውነትዋ ይንቀጠቀጥ ነበር፤ ታለቅሳለች፤ በመሀል ደግሞ ትስቃለች:: ደግማ ደጋግም እጄን ጥብቅ አድርጋ ይዛ

"ሐኪም! አድነኝ!" ትላለች::

የቦምብ ድንጋጤ (Bomb shock) ይዟታል:: ለፈጠን ይህ የመጨረሻው ነገር ነበር:: እልቻለም:: እየጮኸ ድንገት ተነስቶ ዘሎ ወጣ::

ቦምብ ድብደባው እቁሞ ስለነበር እኔም ተነሳሁና አቧራውን አራግፌ ምን እንደሆነ ለማየት ወጣሁ:: የታፈን ጩኸት ከመስማቴ በፊት በየቦታው ፈለግሁ:: ከገደሉ ስር የአንድ ሰው መቀመጫውንና የሚንፈራፈሩ ጥንድ እግሮቹን እያለሁ:: ጠጋ ብዬ ስመለከት የፈጠን እግሮች ናቸው:: ከመጠን በላይ በነበረው ፍርሃት የተነሳ በአለቶች መሀከል ባለ ሰንጥቅ ውስጥ እየተሳበ መግባት ፈልጓል:: ጭንቅላቱን ከንድና እጆቹን ከትከሻው ጋራ ማስገባት ችሏል ነገር ግን ከዚህ በኋላ ተጣብቆ ቀረ:: ወደ ውስጥ መግባትም ሆነ ወደኋላ መውጣት እልቻለም::

ከሌሎች ጋራ በመተባበር ወደ ጎን ካዘርነው በኋላ በሰንት መከራ አወጣነው:: ሸሚዞቹ ተቀዳደዋል፤ ክርኖቹ ትከሻዎቹና ጎኑ ተላልጠው ደም በደም ሆነዋል:: እንዳለው ከሆነ መጀመሪያ ራሱን ሲያስገባ ተረጋግቶ ነበር:: ጭንቅላቱ ከገባ በኋላ ግን በሃሳቡ ዘንዶ ውስጡ ቢኖርስ ብሎ ማሰብ ጀመረ እና ለመውጣት ሲሞክር ተቀርቅሮ በመቅረቱ አስቃቂ ስቃይ ደረሰበት::



የዛን ቀን ቦምብ ድብደባ የስድስት ሰዎች ህይወት ከብዙ ከብቶች ጋር ወሰደ በተጨማሪም ብዙ ሰዎች ቆሰለው ነበር::

ማታውኑ በጨረቃው ብርሃን ደጃዝማች እያሌው ራሳቸው መጡ፤ የደረሰውን ጉዳት ለማየትና የቆሰሉትን ለመጎብኘትና ሰላምታ ለመስጠት ነበር:: ለሁሉም ለቆሰሉት ሰዎች ስጦታ የሚሆን ገንዘብ፣ ልብስ፣ ትኩስ ዳቦ፣ ወተት፣ ጠላ፣ ጠጅ የመሳሰሉት ይዘው መተዋል:: ከሳቸው ጋራ አብረው እየዞሩ እያንዳንዱን ቁስለኛ በመልካም ቃላት በጓደኝነት ሲያናግሩ ማየት ልብ የሚሰብ ነገር ነበር:: እያንዳንዱ ሰው እንዴትና የት ቦታ ላይ እንደቆሰለ ለመዳን ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድበት ከዚያ በኋላስ ቋሚ የአካል ጉዳት ይደርስበት እንደሆን ማወቅ ይፈልጉ ነበር::

የነበርኩበትን መጠለያ ከተመለከቱ በኋላ ሁለት ዋሻዎች ያሉበት መጠለያ ለራሴና ለመስሪያ እንዲሆን እንደሚያገኙልኝ ቃል ገቡልኝ::

በታህሳስ ሀያ ሰምንት በጥዋቱ ስሜን በሚጣራ ሰው ድምፅ ነቃሁኝ:: የኩብር ዘብ ወይም የዘቦቹ አለቃ ፊታውራሪ ነበር:: ማወቅ የፈለገው ነገር ትናትናውኑ ከሰአት በኋላ አውሮፕላን ላይ መተኮሱን አይቼ እንደሆን ነው::

እዎ በርግጥ አይቻለሁ

ከዚያም የመጨረሻውን ጥይት እንደተኮሰበት ወዲያው ጅራትዋ ተገንጥሎ ሲወድቅ እንደተመለከተ ነገረኝ:: ኮማንደሩ የሚነግረኝ አውሮፕላን ተኩሶ እንደጣለ ነው:: ሁለት ሰዎችም ወደቀ የተባለውን ጅራት ሊያመጡ ወተዋል:: በኋላም በእውነትም ሁለት ግዙፍ አገልጋዮች ያልፈነዳ ቦምብ ይዘው መጡ::

በጥንቃቄ ወለል ላይ እንዲያስቀምጡት ነገርኳቸውና ፊታውራሪውን ጅራት የተባለው ነገር ምን እንደሆነ ነገርኩት:: ለማሳመንም ጋዝ ያለበትን ቦታ ብሎን ፈታሁና ተጠንቅቆ እንዲያሸተው ፈቀድኩለት:: ከዚያም ቦምቡን ይዘው የመጡትን ሁለት ሰዎች ለሁለት ሰአታት እንዲከታተላቸው ነገርኩት:: በዚያ ጊዜ ውስጥ ምንም ካልሆን ከአደጋ ነፃ ናቸው ማለት ነው::

ሁለት ሰአት ሳይሞላ አንደኛው አገልጋይ በህመም እየተንቀጠቀጠ መጣ:: በቀኝ በኩል ሰውነቱ ከጭንቅላቱ ጀምሮ እንገቱ፤ ትከሻው፤ በከፊል ከንዱና ጀርባው በአባጭ ተሞልተዋል:: እባጩ ሲከፈትም ብጫ ቀለም ያለው ፈሳሽ ይወጣ ነበር::

አሁን ለመጀመሪያ ጊዜ ሎሳንቲን የተባለ መድሃኒት ለመጠቀም ልሞክር ነው:: ከሎሚና ከሎራይድ ከተባለ ኬሚካል የተቀመመው የጀርመን

መድሀኒት በብዙ መጠን ከአዲስ አበባ ነበር የተላከልኝ:: በርግጥም መድሀኒቱ መሥራት እንደሚችል ተረጋገጠ፤ ሰውየውም ከጥቂት ቀናት በኋላ አገገመ::

በንጉሡ ትዛዝ በምቡ በአዲስ የበሬ ቆርበት ተጠቅሎ ለምስክርነት ወይም ለመረጃ ወደ አዲስ አበባ ተላከ::

በታህሳስ በመጨረሻዎቹ ቀናት በአንደኛው አንድ የኢጣልያ አስረኛ ለህከምና ወደኔ ተላከ:: መቀመጫው በአዲስ ውሀ በቋጠሩ አባጮች ተሸፍኗል:: ይህም የሆነው ከስአታት በፊት በመሰታርድ ጋዝ ምክንያት ነው:: ይህ አስረኛ ከዚህ ቀደም የገለፅኩት በአንዳባጉና ውጊያ በዱላ ተመትቶ ለአንድ ሙሉ ቀን ህሲናውን ስቶ የነበረው ነው::

ከዚያ በኋላ የሆነው ነገር በራሱ አገላለፅ እንደሚከተለው ነው

በታህሳስ ሰባት ወታደሩ ሲነቃ ብርቅ ያለ የከሰአት በኋላ ፀሀይ ነበር:: የነበረበት ሜዳ ባዶ ነበር:: ትንሽ ግራ ተጋብቶ ዙሪያውን በሙሉ ተመለከተ:: በኋላ ግን ምን እንደሆን በአእምሮው ብልጭ አለበት:: ነገር ግን ለጊዜው ትኩረቱ ጥሙን የሚያረካበት ውሀ መፈለግ ነበር:: እያዞረውና ደከሞት ሰባት ኪሎሜትር ከተጓዘ በኋላ ጥልቅ ሸለቆ ውስጥ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ አንደ ትንሽ ወራጅ ውሀ ያለበት ቦታ ይደርሳል:: ውሀ ከጠጣ በኋላ ዛፍ ሥር ቁጭ ብሎ ሲያንሰላስል የሆነውን ሁሉ እና ምን ያህል ጊዜ አእምሮውን ስቶ እንደነበር በርግጠኛነት የማያውቅ ለመሆኑ ውሳኔ ላይ ይደርሳል:: ጓደኞቹ ሰላላነሱት ደግሞ ተሸንፈው የሸሹ ለመሆናቸው ምክንያት ሆኖለታል:: ስለዚህ በአነዚህ ያልሠለጠኑ ሰዎች እጅ እንዳይወድቅ መጠንቀቅ አለበት:: ሕይወቱ ከማለፉ በፊት ሰውነቱን ምን ለማድረግ እንደሚያልሙ ማንስ ያውቃል? ሰለ ጨካኝ ሥራቸው ብዙ ወሬ ሰምቷል::

ለአስር ቀናት እንደሚሳደድ አንሰሳ በየቦታው በቁጥቋጦችና ጫካ መሀል እየተዘዋወረ ሰነበተ ህይወቱን ለመጠበቅም ሥራስር እና አንቁራሪት እየበላ ውሀ አየጠጣ ነበር:: ቀስ ብሎ ግልፅ የሆነለት ነገር ቢኖር ውሎ አድሮ የዱር አራዊት ሰለባ እንደሚሆን ነው:: ለከፋም ለደጉም በአካባቢው ወዳሉ ገበሬዎች ወደ አንዱ ለመሄድ ወሰነ::



መጨለም ሲጀምር ቀረብ ወዳለው ወደ አንድ ቤት ሲሄድ በንዴት ከሚጮሁ ጥንድ ውሾች ጋራ ይገጣጠማል:: በዚህ ጊዜ ገበሬው ሁኔታውን ለማጣራት ይወጣል:: ገበሬው በመገረም ሲመለከት ጊዜ ወሰደበት:: በኋላ ግን ጣልያናዊው የፈለገውና የሚጠይቀው ትንሽ ምግብ መሆኑን ከጣልያኑ የሰውነት ምልከት ይረዳል::

በቤቱ ውስጥ የነበረ የአቢሲኒያ ወታደር ደግሞ ሁኔታው ምን እንደሆነ ለማየት ይወጣል:: ልከ ጣልያናዊውን እንዳየው ለመማረከ ተንደርድሮ ሲሄድ ገበሬው ያሰበው አሱኑ ስለነበር ሁለቱ ጭቅጭቅ ይጀምራሉ:: ጭቅጭቁ ጠንከር ማለት ሲጀመር እያንዳንዳቸው ጣልያናዊውን ወደ ተለያየ አቅጣጫ መጎተት ጀመሩ:: በመጨረሻ ገበሬው የያዘውን ለቆ ወደ ቤቱ ገባና የተቀባበለ ጠመንጃ ይዞ ወጣ:: ሌላኛውም ነገሩ ገባውና ወደ ቤት ገብቶ የራሱን ጠመንጃ ለመያዝ ሲሞከር ትንሽ እርምጃ ሳይራመድ ተኩሰ ተተኮስ ወታደሩ በሙሉ ሰውነቱ መሬቱ ላይ አንዳለ ወደቀ::

በሚቀጥለው ቀን የኢጣልያው ወታደር ወደ ሠፈር አለቃው ተወሰደ:: አለቃውም ወደ ደጃዝማች አያሌው እንዲወስደው ነበር የታሰበው:: ነገር ግን ሁልጊዜ እንደሚሆነው ሁሉ ዘገየ:: ጣልያናዊው ጭብጥ የአተር ንፍሮ አየበላ ለብዙ ቀናት መቆየት ነበረበት::

በመጨረሻም የሠፈር አለቃውና ጣልያናዊው መንገድ ሲጀምሩ ጣልያናዊው ለአጭር ጊዜ ከመንገድ ወጣ ብሎ መሄድ እንደሚፈልግ ተናገረ:: ነገር ግን አቢሲኒያዊው ሰላልገባው ዝም ብለው መንገድ ሲቀጥሉ በገና ዋዜማ የጋዝ ቦምብ የተጣለበት ቦታ ይደርሳሉ:: (ይህንን ቦታ ግን አሳጥሬ በአማርኛ መርዝ አለ የሚል ምልከት በትልቁ አስፅፌ ተከየበት ነበር) አደጋ መኖሩን ሳይጠራጠር ጣልያናዊው አጥሩ ውስጥ ገብቶ ለመፀዳዳት ተንቆራጠጠ::

ከሁለት ሰአታት በኋላ ደጃዝማች አያሌው ፊት ሲቀርብ አቢሲኒያኖቹ አሰኪገርማቸው ድረስ ይዘልና ይጮህ ነበር::

# ምዕራፍ አሥራ አምስት

## የካምፕ ኑሮ

በጥር ሰባት ድሬሰሮችና የቆሰሉት ሰዎችን ጨምሮ ደጃዝማች አያሌው ወደ ሰጡን ዋሻዎች ቦታ ቀየርን፡፡ ዋሻዎችም ከሳቸው ዋሻ አጠገብ ነበሩ፡፡ ጥሩ ቦታ ነው የተመረጠው፡፡ ብዙ ዛፎች ባሉበት ትልቅ ሜዳ መሀል በጎንና በጉኑ ቀጥ ያለ ገደል ያለበት ሸለቆ የሚጀምርበት ቦታ ነው፡፡ መውጫቸው ወደ ሸለቆው አቅጣጫ የሆኑ አሥራ ስምንት ዋሻዎች በተርታ ይገኙበታል፡፡ የዋሻዎቹ ጣራ ከእሳት ገሞራ የወጣ ፍም በሶስት እስከ አራት ሜትር ውፍረት ደርቆ የተጋገረበት ነው፡፡ የአብዛኛዎች ዋሻዎች መግቢያዎች በትልልቅ ዛፎች የተሸፈኑ ናቸው በለዚህ ከላይ ከአየር ላይ መታየት አይችሉም፡፡ በለዚህ ከማንኛው የአየር ጥቃት መከለል እንችላለን፡፡ ቦምቦቹ ወይ ሜዳው ላይ አለዚያም ሸለቆ ውስጥ ነው የሚወድቁት በሁለቱም ቦታ ቢወድቁ እኛ ላይ ጉዳት አያደርሱም፡፡

ከዋሻዎቹ ትልቅ ስፋት ያለው ለዳጃች አያሌው ምግብ አዳራሽ እና እንግዳ መቀበያ ሆኗል፡፡ ስፋቱም ሰላሳ ሁለት ሜትር ርዝመት የጎን ስፋት ስምንት ሜትርና ከፍታው ደግሞ ስድስት ሜትር ነበር፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ስፋት ያለው ደግሞ ሆስፒታሉ ነው ያም ሰላሳ በሽተኞች የሚያስተኛ ሆኖ ለክሊኒክ ሥራ ቦታ ነበረው፡፡ እነዚህ ዋሻዎች በአንድ በኩል ግድግዳ ስላልነበራቸው የግማሽ ሜትር ከፍታ ያለው ግንብ በድንጋይ ተሠርቶ ላዩ ላይ አሸዋ የተሞላበት ከረጢት እንዲደረደርበት ተደረገ፡፡

የኔ መኖርያ የነበረው ለአልጋ መኝታ የሚሆን የተፈጥሮ ኪስ ቢጤ ነበረው፡፡ ከፍሉንም በእቃ መያዣ ሳጥኖች ከተሰራ ሶፋ ፤ እቃ መደርደሪያ እና ጠረጴዛ በማስገባት አደራጀሁት፡፡ ሀያ ስድስት ካሬ ሜትር ስፋት ያለው ደጃች አያሌው የሰጡኝ የፋርስ ስጋጃ ወለሉን በአብዛኛው ሸፍኖታል፡፡ በየቀኑ ጠዋት ጠዋት የኔ ሰራተኛ አዲስ አበቦች እየቀጠፈ በጠርሙስ አድርጎ ጠረጴዛው ላይ ያስቀምጣል፡፡ ይህንን ደግሞ ራሱ አስቦ ነበር የሚያደርገው እና አበተጓጉሎም አያውቅም፡፡



በዚህ ቦታ ለሁለት ወራት ያሳለፍኩት ጊዜ በጣም ደስተኛ የነበርኩበትና በጦርነቱ ጊዜ የሚበቃ እረፍት ያገኘሁበት ነው፡፡ የነበረው ሥራም አጣዳፊ ወይም አደገኛ አልነበረም፡፡ በየቀኑ ከጠዋቱ አራት ሰአት ላይ አዲስ በቦምብ የቆሰሉ ሰዎች ይመጣሉ ይህ ግን የሥራዬ አንዱ ክፍል ነበር፡፡ ከደጃች አያሌው ጋራ ጠንከር ያለ ወዳጅነት ነው የነበረኝ፡፡ ደጃዝማቹ ለኔ የጎደለብኝ እንጂ የተሟላላኝ እንዳልሆነ አድርገው ነው የሚያስቡት፡፡ ከዋሻዬም ጋራ በጣም ተላመድኩ፡፡ ጥሩ ምግብ ይመጣልን ነበር፡፡ ጤንነቴም እንደዚያን ጊዜ ተስማምቶት አያውቅም፡፡ ለብዙ አመታት ያሰቃየኝ የነበረው ወባ ለቆኛል፡፡

አንድ የሚያሳስበኝ ነገር ቢኖር ከቤተሰቦቼ ምንም አይነት ወሬ አለመስማቴ ነው፡፡ በሃሳቤ የሚመጣው የባለቤቴና ልጆቼ የወላጆቼና ቤተሰቦቼ ናፍቆት ነው፡፡ ነገር ምንም የሚደረግ ነገር አልነበረም አውቄ የገባሁበት ነገር ስለሆነ መቻል ነበረብኝ፡፡

በዚህ ጊዜ የነበረው በጠቅላላው ጦር ውስጥ የሚታየው ወደር የሌለው ግድየለሽነት ደግሞ እኔንም ይነካኛል፡፡ ከውጭ የምንሰማው ትንሽም ወሬ ቢሆን ጥሩ ነበር፡፡ ተስፋ የተጣለው ጣልያኖቹ ላይ የተጣለው ማዕቀብ ሥራውን እንደሚሰራና ጣልያኖችም መሳሳታቸውን አይተው ሰላም እንደሚፈጥሩ ነበር፡፡ ከአዲስ አበባ በሚላከው የውሸት ዘገባ መቀሌ በጦር ሚኒስትሩ እጅ ተመልሶ መያዙ ያለምንም ጥርጥር የተቃረበ ነገር ይመስላል፡፡

ጊዜው ረዥም ሆኖ እልታየኝም ምክንያቱም የነበረኝን ትርፍ ጊዜ የምጠቀምበት ሌላ ሥራ አግኝቻለሁ፡፡ ባንክ ሠራተኛ ሆኛለሁ፡፡ ብዛት ያለው የወረቀት ገንዘብ ነበር፡፡ አብዛኛው የኢጣልያ ሊሬ ነበር፤ ዋጋውም በቀን ሁለት ሶስት ጊዜ ወደላይ ወደ ታች ይወርድ ነበር፡፡ ያም በየቀኑ በሚወራው ጣልያኖች ላይ በተጣለው የኢኮኖሚ ማዕቀብ የተነሳ ነው፡፡ አዲስ ሰላይ መጥቶ በቅርቡ ሰላም ሊፈጠር ነው የሚል ከሆነ የሊሬው ዋጋ ወደ ላይ ይወጣል፡፡

የሚገርመው ነገር የጣልያኖች ሊሬ የአንድ ሺ ብር ኖት በአንድ ጊዜ ይሸጥም ይገዛም ነበር፡፡ በመጀመሪያ አንድ ሺ ሊሬው ሶስት ማርትሬዛ ነበር የሚያወጣው በኋላ ግን ወደ ሀያአምስት ከዛም ወደ ሰላሳ ከፍ እያለ መጣ፡፡ ብዙ ጊዜም ወደ አከሱም ለራሳቸው የሚበቃ ትርፍ በሚወስዱ በሰላዮችና በነጋዴዎች በኩል ተልኮ ወደ ማርትሬዛ ይቀየር ነበር፡፡ ሰዎቹ ከወረቀቱ ይልቅ የሚያቃጭለውን ማር ተሬዛ ነው የሚፈልጉት፡፡

እያደገ የመጣው የሊሬ ዋጋ በኔ አስተሳሰብ ከአቢሲኒያ እየተባባሰ ከሚሄደው ውድቀት ጋራ የተያያዘ ነበር::

ለአቢሲኒያኖች በገንዘብ የመጣ ነገር የራሳቸውን ዘመዶች አለማማን የተለመደ ነገር ነው:: ከነሱ ይልቅ ነጭ ሰው ላይ ሙሉ እምነት ነበራቸው:: ሌላ ሰው ገንዘባቸውን እንዳይሰርቅባቸው ሊፈሩ እኔን እደራ ጠባቂ አደረጉኝ:: ቁልፍ ያለው ሳጥን እንደካዝና ሆነ:: በአብዛኛው ጊዜ እስከ መቶ ወይም መቶ ሃምሳ ሺ ሊሬ ድረስ ይይዝ ነበር:: ሳጥኑ በየጊዜው ይቆለፋል ይከፈታል ምክንያቱም ሁሉም ሰው ገንዘቡን ከመቅበር ይልቅ መነገድና ማትረፍ ይፈልግ ነበር::

ከሁሉም አደገኛው ነጋዴ የኔው ሠራተኛ ነበር:: የብዙ ወራት ደሞዙን አስቀድሞ ወስዶ ግን ወዲያው ጨርሶታል:: አንድ ቀን የአስር ብር ብድር ይጠይቅና ይወስዳል:: በዚህ በተሠጠው ብር ይነግድበትና ከአንድ ወር ተኩል በኋላ የኮራ የአራት መቶ ብር ባለቤት ይሆናል:: ይህ ንግድ ሥራ ረድቶታል የንግድ እውቀቱ ወይም ችሎታው አሌ የማይባል ነገር ነው::

ለጠሩ ታማኝ የባንክ ሠራተኛ ሆኜ መሥራቱን በደስታ የማደርገው ነገር ነበር:: አንዳንድ ጊዜ ግን ከማያቆመው የብርና ሊሬ ውይይት ውጭ በሌላ ነገር እአምሮዬን ብወጥረው እመኘ ነበር:: መፅሐፍ ቅዱሴን ይዣለሁ ግን የነበረኝ አንድ መፅሀፍ እሱ ብቻ ነበር::

አንድ ቀን ማታ ምን እንደሆነ ያላውቅኩት ነገር ይሰማኝ ጀመር:: ከውጭ የሚያምር የጨረቃ ብርሃን ስለነበር እንደ ሁልጊዜዬም እንቅልፍ ነሳኝ:: ከነልብሴ አልጋዬ ላይ ተጋደምኩ:: ስለ ሁሉም ነገር አሰብኩኝ፤ የቀረኝም ነገር አልነበረም::

ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ጭንቅላቴ ውስጥ የሚመላለስ ዜማ መኖሩን አውቅሁኝ:: ከሎንገሪን የግራል ታሪክ ነበር::(የስዊድን አገር ዜማ ነው):: አሁን ምን እንደሆነ ስላወቅሁ እንደገናም የምወደው ሙዚቃ ስለሆነ ተነሳሁና ግራማፎኑን ማጫወት ጀመርኩ ነገር ግን ከጥቂት ጊዜ በኋላ የዚህ አይነት ሙዚቃ በቃኝ:: በንዴትም ሶስቱን የሙዚቃ ሬከርዶች ግድግዳው ላይ ወረወርኳቸው::

የኔ ሠራተኛ በድምፁ ነቅቶ እንደተያቄ ምልክት ተጣሞ ቆሟል:: ጌታው በድንገተኛ እብደት ተለከፎ ይሆን ብሎ ያሰበ ይመስላል::

"ሀብቴ! በገና ደርዳሪውን ጥራውና እንዲጫወትልኝ" በአምስት ደቂቃ ውስጥ በገና ደርዳሪው ከባለአስር ክር በገናው ጋራ ከተፍ አለ::



ብዙ ነጮች አፍንጫቸውን ነፍተው ከአፍሪካ ተወላጆች ደስ የሚል ሙዚቃ ደግሞ አለ ወይ ብለው ያስባሉ:: እንግዲህ ሙዚቃ የመንፈስና የሕይወት መግለጫ ከሆነና እያንዳንዱ ሰው ደግሞ ከየትም አገር ይኑር ጥሩና ደስ የሚል ነገር በመንፈሱ ሊኖረው እንደሚቸል አንድ ሰው ከተቀበለ ከሙዚቃ ላይ የአቢሲኒያን ሙዚቃ ጨምሮ የውበት ብልጭታ ሊኖር እንደሚችል መጠበቅ አለበት::

የአቢሲኒያውያን በገና ደስ የሚል ነው:: በተለይ አንድ ሰው ለሰለሰ ካለና ደስ ከሚለው ሙዚቃው ጋር አብሮ የሚሄድ ትክክለኛ የውስጥ ስሜት የሚኖረው ከሆነ:: ከዚያ ሁሉ በፊት ግን አንድ ሰው ከሙዚቃው ጋራ አብረው የሚወርዱትን ቃላቶች መረዳት መቻል አለበት:: ይህም የሚሰማው ሙዚቃና የሚደረደረው ግጥም ያልተሰማሙ ወይም የሚጋጩ እንዳይመስል ነው::

አቢሲኒያውያን ሌሎች የራሳቸውን የሙዚቃ መሳሪያ ሲሰሙ አረፈት ቢስ ወይም ቁንጥንጥ ናቸው:: ነገር ግን በገና ሲሰሙ ትልቁም ሆነ ትንሹ በፊሪሀ ነው የሚያዳምጡት:: አልፎ አልፎም በጉንጮቻቸው ላይ እንባ ይኮላል:: በገና የሚደረደረው አልፎ አልፎ ነው ያውም በማታ ነው:: የሚጫወቱት ሰዎች ደግሞ ባለሙያተኞች ብቻ ናቸው:: ያን ቀን ማታ ወዳጄ አስፋው እንደዚህ አድርጎ ተጫውቶም አያውቅም። ወይስ እኔ ብቻ ነኝ እንደዛ ያሰብኩት?

መጀመሪያ ከዳዊት መዝሙሮች አንዱን ተጫወተ:: ቀጥሎም ስለፈጣሪ መሀሪነትና ጠባቂነት፤ ስላለፉ ጀግንነት ሥራዎች፤ አንዳንድ ጊዜ በዘመናቸው የተሳካላቸውን የጀግኖች ታሪክ ከመፅሐፍ ቅዱስ በመጥቀስ ሌሎች ተስፋ አስቆራጭና መድረሻ በሌለው ሁኔታ ትግላቸውን የቀጠሉትን በማውሳት ተጫወተ:: አስፋው ሁሉም ነገር ሀላፊ መሆኑን በማስታውስ ዜማውን ጨረሰ::

በአባ ዳኘው ጊዜ (የሚኒሊክ መጠሪያ)
አባቶቻችን ያላዩት ነገር ሆነ
ውሃ ወደዳገት ወጣ
ሽበዎች ተናገሩ
ባቡርም ተነዳ
ምኒሊክ ፈጣሪን መሰለ ወይ? ብሎ ልቤ ዋለለ
ያም ሆኖ ምኒሊክ ካለፉት ጋር አለፈ
ሁሉም ነገር ጊዜያዊና ሀላፊ ነውና

አንድ ቀን አንድ ከፍተኛ ባለሥልጣን ከአዲስ አበባ መጣ:: የተላከውም በንጉሡ ትዛዝ በጦር ሚኒስትሩ በኩል ነው:: ሰውየው እንደሚለው በእንዳባጉና በተገኘው ድል እያሌውን እንኳን ደስ ያለህ ለማለት ነው የመጣው:: በኋላ ሲጣራ ግን የመጣበት ጉዳይ የተወራው የድል ወሬ እውነት መሆኑን ለማጣራት ሀላፊነት ወስዶ ነው:: ጠላት በታህሳስ ስድስት የተገኘውን የአቢሲኒያውያን ድል ከዷል:: ስለዚህ በአዲስ አበባና በሌሎች ግንባሮች ደጃች አያሌው የላኩት የድል መልከት ጥርጣሬ ውስጥ ወድቋል::

ሳምንቱን በሙሉ ባለሥልጣኑ የጦር ሜዳ ውጊያውን ሲያስስ ሰነበተ:: ሜዳ ላይ ያልተነሱት አስከሬኖችን እየቆጠረ መዘገበ፤ ታንኮችንና ሞተራቸውንም መዘገበ:: ከዚህ በተጨማሪ ሁለት ጆንያ ሙሉ ኮፍያዎች፣ ኮከቦች፣ ትከሻ ላይ የሚደረጉና ሌሎችም የወታደር ምልከቶቸ ከሞቱ የኢጣልያ መኮንኖች ሰበሰበ::

ይህ ባለስልጣን በሌሎች ግንባሮች ሁሉም ነገር በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደ ነው በማለት እኛን ለማረጋጋት ሞከረ:: እንደሱ አባባል ራስ ካሳ ጣልያኖች ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰው አብይ አዲንና ተምቤንን ስመያዝ እያመሩ ነው:: ራስ ሙሉጌታም ቢሆን መቀሌን ለማጥቃትና መልሶ ለመያዝ አመቺ ሁኔታ እየጠበቁ ነው:: ወታደሮች ብዙ የአየር ጥቃቶች ደርሰባቸዋል ቢሆንም ወኔያቸው በጥሩ ሁኔታ ነው ያለው:: የወታደሩ ስንቅም እያሰቀ ነው በአንዳንድ ቦታ ገበሬዎች በራባቸውና ስነ ሥርአት በጎደላቸው ወታደሮች እየተመዘበሩ ነው:: የጦር ሚኒስትሩ ራስ ሙሉጌታና ራስ ካሳ ግን በጥሩ ሁኔታ ነው የነበሩት:: የሚበቃ ምግብ ነበራቸው:: የሚኖሩበት ጥሩ መጠለያ ዋሻ ግድግዳው በከፈይ መጋረጃ ተሸፍኗል በየቀኑም ሻምፓኝ ይጠጡ ነበር::

በኛ ግንባር ምስጋና·ለደጃች አያሌው አርቆ ማሰብና ድርጅት ይሁንና ጦሩ የአስፈሳጊ ነገሮች እጥረት አላጋጠመውም:: ለአምስት አመታት እህል እየሰበሰቡ ተከዜ ወንዝ ጥግ ድርስ ከዝነዋል:: ጦርነቱ እንደሚመጣም እርግጠኛ ነበሩ:: የሳቸው ጦር ከነዚህ የእህል ካዝናዎች በየሶስት ቀናት ሌላ ዙር ስንቅ ይታደሰዋል::

የኛ ካምፕ ባለበት አካባቢ ያሉ ገበሬዎች ምንም አይነት ረብሻ እንደማይደርስባቸው ደጃዝማቹ ቃል ገብተውላቸዋል:: አንድ ጊዜ ብቻ ሁለት ወታደሮች በጉልበት የገበሬ ቤት ውስጥ ገብተው የገበሬውን የቤት እቃ ወስደዋል:: እነሱም ለፍርድ ቀርበው የሞት ፍርድ ተፈረደባቸው::



ቄሱ ጣልቃ ገብተው የሞት ፍርዱ ወደ ግርፋት እንዲቀየር ተማፅነው አሰቀይረውላቸዋል:: አመሻሽ ላይ አጥፊዎቹ እንዲቀርቡ ተደረገ:: እጃቸውም ታስሮ ነበር:: የሠረቁት ዕቃም አንገታቸው ላይ እንዲንጠለጠል ተደረገ ከዛም ከካምፕ ወደ ካምፕ እየዞሩ እንዲወሰዱ ተደረገ:: አብሯቸው የሚሄደው ቀጪው ደግሞ በየአጋጣሚው ባለ በሌለ ሀይሉ በአለንጋ ይለመጥጣቸው ነበር:: በእያንዳንዱ ግርፋት ደግሞ

"ሠርቄያለሁ! እኔን ያየህ ተቀጣ" እያሉ መጮህ ነበረባቸው::

ደጃዝማች አስቀድመው የቄሱን ሽምግልና ገለል ለማድረግ ወስነዋል:: ስለዚህ በቅጣቱ ላይ እያሉ በጎን መላከተኛ ልከው ቀጪውን የሌቦቹን ሕይወታቸወን እንዳያሰተርፍ መከረውታል:: ከአራት መቶ ግርፋት በኋላ አእምሮአቸውን ሳቱ:: አንደኛው ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሞተና ተወሰደ:: ሌላኛው ሰው ግን የት እንደደረሰ እላወቅንም::

ገበሬዎቹም በጣም ተደሰቱ ደጃዝማች አያሌውን አሞገሱ:: በሳቸው ወታደሮች እንደማይመዘበሩ እርግጠኛ ነበሩ:: ነገር ግን ደስታቸው ለአጭር ጊዜ ነበር:: የራስ እምሩ ሠራዊት ይዞት የመጣውን ስንቅ ጨርሷል:: ደጃች አያሌው ደግሞ ከተከዜ ማዶ ካከማቹት እህል እንዲወስዱ ቢጋበዟቸውም ተከዜ ማዶ ሄደው እህል ለመውሰድ ሰንፈው ነበር::

በዛ ፋንታ ከጎጃም የመጣው የራስ እምሩ ጦር የአካባቢውን ገበሬ ቤት መውረርና መመዝበር ጀመረ:: ብዙ ጊዜ በገበሬውና በሠራዊቱ መሀል ውጊያ ተደርጎ ብዙ ሰዎች አለቁ:: ገበሬዎቹ ግንባር ፈጥረው ንብረታቸውን ከእንዳባጉና በወሰዷቸው ጠመንጃዎችና ቀላል የአውቶማከ መሳሪያዎች ለመከላከል ወስነዋል:: ሰላሳ የሚሆኑ የራስ እምሩ ወታደሮች ከሞቱ በኋላ ገበሬዎቹ ሰላም አገኙ::

ነገር ግን አንድ ሰው በዚህ በታየው ጉድለት ምክንያት የጎጃም ሰዎች ላይ መፍረድም የለበትም:: ከረጅም ጊዜ መቦዘን በኋላ ለጦርነት በነበራቸው ጉጉት ምክንያት ጦርነት ለመጫር ሰበብ ነበር የሚፈልጉት:: አንድ የራስ እምሩ ፊታውራሪ ከሶስት ሺ ሰዎች ጋራ ሆኖ እስከ አከሱም ድረስ ቢጓዝም ተቃዋሚ ወይም ጠላት አላጋጠመውም:: ጣልያኖቹ ለሶስት ቀናት ሙሉ ባደረጉት ጀሮ በሚያደነቁር የመድፍ ድብደባ ሰለረኩ ከአከሱም ወጣ አላሉም::

ስለ ራስ እምሩ የጦር ሚኒሰትርና ተወካያቸው ስለነበረው የሀያ ሁለት አመት ወጣት ዮሐንስ ሳልናገር ማለፍ አልችልም:: ወጣቱ በአንድ እንግሊዛዊ

በባሪያ ንግድ አሰበት ተብሎ ተከሶ ለሶስት አመት አዲስ አበባ ከታሰረ በኋላ ሲፈታ የራስ አምሩን ጦር የተቀላቀለ ነው፡፡ ሁለት ጊዜ ከደጃች አያሌው ጋራ ስለ ጦርነቱ ዕቅድ ለመወያየት ተልኮ ቢመጣም በመጣ ቁጥር ደጃች አያሌው ስለ አቢሲኒያ በጣም ወሳኝ ጉዳዮች ልምድ ከሌለው ወርበሳ ወጣት ጋር መወያየት ደስተኛ ስላልነበሩ ፊት ነስተውት ካከምፑ ይባረር ነበር፡፡

በየካቲት መጀመሪያ ላይ ዮሐንስ በድሮው በኤርትራ ድንበር ከመረብ ወንዝ አጠገብ ራማ በተባለ ቦታ ስለ ሰፈሩ የጣልያን መንገድ ሰሪዎች ቡድን ወሬ ይሰማል፡፡ ጣልያኖቹ ራማ ከጦርነቱ ቦታ ሃምሳ ኪሎ ሜትር ርቀት ወደኋላ ስለሆን የሚያሰጋ ነገር የለም ብለው ይጠብቋቸው የነበሩት አንድ ሺ ወታደሮችን ወደ ሌላ ቦታ ወስደዋቸዋል፡፡

አንድ ቀን ከሰአት በኋላ ዮሐንስ ሶስት መቶ ሥርአት አልባ የሆኑ ወታደሮች ይዞ ራማ ላይ ጥቃት ለማድረስ መንገድ ይጀምራል፡፡ ዙርያ ጥምዝ መንገድ ስለወሰደ ርቀቱ ወደ ሰባ ኪሎሜትር ተራዝሞ ከሌሊቱ አስር ሰአት ሲሆን ከቦታው ይደርሳል፡፡

አምስቶ መቶ የሚሆኑት ሠራተኞች ጠባቂ ሳያቆሙ ካምፑ ውስጥ ተኝተው ነበር፡፡ የሚጮሁት አቢሲኒያኖች በየድንኳኑ እየገቡ በጥይት የደረሱበትንም በጎራዴ ይቆርጣሉ፡፡ አብዛኛዎቹ ለመነሳት ጊዜ ሳይኖራቸው የተኙበት ላይ ነው የተገደሉት፡፡ ኢንጂነሩ ብቻ ነበር የታጠቀው፡፡ እሱም ሚስቱንና ልጆችን ለመከላከል አጥብቆ የአንበሳ ያህል ተዋጋ፡፡ ሶስት ጥይት ሲቀረውና ምንም ተስፋ ያለው ነገር አለመሆኑን ሲያውቅ መጀመሪያ ልጁን ከዚያ ሚስቱን ተኩሶ ከገደለ በኋላ በሶስተኛው ጥይት ራሱን ገደሰ፡፡ ያገሩ ተወላጅ የሆነችው ሠራተኛው ደግሞ አልቀረላትም በጎራዴ ተገደለች፡፡

ሰማንያ የኢጣልያ ሠራተኞች ተገድለዋል፡፡ የቀሩት ከአራት ከተማረኩት ውጭ በሙሉ በየጫካው ሸሽተው አምልጠዋል፡፡

አጥቂዎቹም ጉዳት ሳይደርስባቸው ከውጊያው አልተመለሱም፡፡ ዳይናሚት ያሰበት ሳጥን ፈንድቶ ብዙ ሰዎች ሞተዋል፡፡ በኋላ ደግሞ ካምፑ ሲዘረፍ አርስ በርስ እየተጣሉ ተተኳኩሰዋል፡፡ የቀሩት ዘጠና አምስት የሚሆኑት የተረፉት ወታደሮች የሞቱትን ወንዶች እየሰበቡ ሁሰቱን የተገደሉ ሴቶችን ጡቶች ቆርጠዋል፡፡

የራስ አምሩ የጦር ሚኒስትር ዮሐንስ በዚህ አሰቃቂ የሚያሳፍር ድርጊት ያገኘው ነገር አልነበርም፡፡ ሁሉም በተፈፀመው ድርጊት ደስተኛ አልነበረም፡፡ በተጨማሪም በኛ ወገን በኩል በዚያን ጊዜ የተፈፀመው መሰሰብ ለመጀመሪያም ለመጨረሻ ጊዜ እንዲሆን ሆነ፡፡



# ምዕራፍ አሥራ ስድስት

## የነጋሽ ስማቸውን መመለስ

የደጃች አያሌው ወታደሮች በምግብ በኩል አጥረት እንዳልነበራቸው ገልጫለሁ፡፡ በልብስ ሲመጣ ግን ከጥር ጀምሮ ሁኔታቸው በጣም የሚያሳዝን ነበር፡፡ ብዙዎቹ እራፊ ብቻ ነበር የለበሱት፡፡ ደጃዝማች እያንዳንዳቸው ሀያ ሰባት ሜትር ርዝመት ያለቸው ከጥጥ የተሰሩ ሁለት ሺ ጣቃ ጨርቅ ከሱዳን እንዲመጣ አዘው ነበር ነገር ግን ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ ጨርቁ አልመጣም፡፡ ከአከሱም በሹልከታ የሚመጣው ልብስ ደግሞ ዋጋው በጣም ውድ ስለነበር ተራው ሰው አንድ መለወጫ ልብስ እንኳን ለመግዛት አቅም አልነበረውም፡፡

ውሀ እንደልብ እያለ ወታደሮቹ ያሳቸውን ልብስ ማጠብ አልፈለጉም፡፡ ምክንያቱ በከፊል ጨርቁ ሲታጠብ ጭራሹን ስለሚበጣጠስ ሲሆን ሌላው ምክንያት ደግሞ የአውሮፕላን ጥቃቱ ነው፡፡

የዚህ ውጤት ደግሞ ጊዜ ሳይፈጅ መታየት ጀመረ፡፡ የሰውነት ቅማል መራባት ጀመረ፡፡ ወታደሮቹ ሰውነታቸውን እስኪደማ ድረስ ማከክ ጀመሩ እጃቸው የማይደርስበትን የሰውነታቸውን ከፍል ከግንድ ወይም ድንጋይ ላይ እየተጠጉ ያሹት ጀመር፡፡ ይህም በየቦታው የሚታይ ድርጊት ነበር፡፡ ተባዩ እየረገፈ በየቦታው ይርመሰመስ ነበር፡፡

የኔ የግል ሠራተኛ በሚደነቅ ጉብዝና ያለኝ የሌለኝ ልብሶቹን በውሃ አፍልቶ አጠባቸው፡፡ ግን ምን ጠቀመ? አዲስ የታጠቡትን ልብሶች ለአንድ ቀን ከለበስኩ በኋላ ሀብቱ ከልብሴ ላይ ቢያንስ ቢያንስ ደርዘን የሚሆኑ ተባዮችን ለቀምኩ ብሎ ይፎክራል፡፡ በኛ በኩል የነበረን አማራጭ ከመጠን በላይ እንዳይራቡ ለማድረግ በየቀኑ መልቀም ነው፡፡ ለአንድ ቀን እንኳን ማሳለፍ አንችልም፡፡ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው የመሻገር ችሎታቸው ወደር የለውም፡፡ ለጥቂት ጊዜ ተባዩ ከላበት ሰው ልብስ ጋራ ከተነካካሁ ከሰውየው ልብስ ወደ እኔ ለመሻገር በቂ ጊዜ ያገኛሉ፡፡

በነዚህ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ተባዮች ምክንያት የተሰቦ ወረርሽኝ ሊነሳ ይችላል ብዬ ሁልጊዜ እንደሰጋሁ ነበር፡፡ ያ ከሆነ ደግሞ የኛ ሠራዊት አለቀለት ማለት ነው፡፡ በሁለት ሳምንታት ውስጥ መዋጋት የማንችልበት ደረጃ እንደርስ ነበር፡፡ ምናልባትም እንዳለ እንደመሰለ ነበር፡፡ በተአምር ግን ከዚህም ሆነ ከሌላ ወረርሽኝ አመለጥን፡፡ አንድ ሰው ብቻ የአሜባ ተቅማጥ ይዞት ተገኘ እሱም ወደ ሌሎች እንዳያሻግር ተከልሎ እንዲቀመጥ ተደረገና ከህክምና በኋላ ወደ ቤቱ እንዲመለስ ተደረገ፡፡

ከአይን በሽታዎችና አልፎ አልፎ ከሚከሰት የወባ በሽታ ውጭ ወታደሮቹ ጤንነታቸው የተጠበቀ ነበር፡፡ ለዚህም ብዙ ምክንያቶች ነበሩ፡፡ የአየር ፀባዩ፤ በብዛት ጊዜን ከቤት ወይም ከዋሻው ውጭ ማሳለፍ፤ በቂ ምግብ መኖር፤ የሚበቃ ቀዘቃዛ ወራጅ ውሀ በበቂ መጠን መኖርን ይጨምራል፡፡

በዛው ልክ ደግሞ የቁንጫ ችግር፤ ዝምቦች እና ደግሞ ቡጀሌ አሰቸግረውን ነበር፡፡ *ቡጀሌ የሚያመጡት ተባዮች በአይን የማይታዩ ጥቃቅን ናቸው፡፡ ከደቡብ አሜሪካ ከሀምሳ አመት በፊት ነው የመጡት አሁን ግን በአፍሪካ ተሰፋፍተዋል፡፡ ይህ ተባይ እንደቁንጫ የመሰለ ሲሆን ሴት ፆታ ያላት ተባይ በሰውነት ውስጥ በርቡራ ከገባች በኋላ አንቁላሏን ግን ወደ መግቢያው አዙራ ነው የምትጥለው፡፡ ብዙ ጊዜ የአገሬው ሰዎች እግራቸው ላይ ነው የምትገባው፡፡ አቢሲኒያኖች ተባዩን በመርፌ በማውጣት የተካኑ ናቸው፡፡ ችግሩ ግን ሌላ አይነት ልከፍት (ኢንፌክሽን) እየተከተለ ያሰቸግር ነበር፡፡ እግር ያብጥና ህመም ስሜት ሰላለው አንድ ለው መራመድ ያቅተዋል፡፡ እኔ ራሴ አንኳን በዚሁ ችግር ለአንድ ሳምንት የአልጋ ቁራኛ ሆኜ ነበር፡፡ እኔ ግን ውጭም ሆነ ዋሻው ውስጥ በባዶ እግሬ ሄጄ አላውቅም ነበር፡፡ ጦርነቱ በትንሽ ወራት ቢራዘም ኖሮ አንድ ሶስተኛው የሚሆነው ሠራዊት በዚህ በቡጀሌ ምክንያት መዋጋት አይችልም ብዬ እፈራ ነበር፡፡

---

*ስለ ቡጀሌ ከተነሳ በአንድ አካባቢ ስለዚች ተባይ የሚገጠም ግጥም እናካፍል፡፡
ሰሟን አማከለች ድንቁ ብለው ነው የሚጠሯት፡፡

አማከለች ድንቁ ነብሰሽን አይማረው
እግሬ ቆሞ ቀረ መሄድ እያማረው

ቡጀሌን በደንብ ፈርፍሮ ማውጣት ሳይቻል ሲቀር የሚገጠመው ደግሞ የሚከተለው ነበር

በዱማ መርፌ ቁልፍ ሲገፉኝ ሲገፉኝ
ባለ ደረባ ቤት ባለፎቅ አረጉኝ፡፡



በገና ዋዜማ ከተጣለብን የመርዝ ጋዝ ቦምብ በተጨማሪ በጥር አሥራ አራትና ሀያ ሰድሰት የመርዝ ጋዝ ቦምብ ተጣለብን፡፡ በመጨረሻው ቀን አርባ ሰዎች ቆሰሉ፤ አንድ ሰው ብቻ ሞተ፡፡ መርዝ በወደቀበት ቦታ ሳር ሊለቅሙ ስለነበር ብዙ የጭነት ከብቶች ሞቱ፡፡

አፍንጫቸው ምላላቸው እና ጉሮሮአቸው ያብጥና ትንፋሽ ይዘጋቸዋል፡፡ ለአንዳንዶቹና ቀለል ያለ ሁኔታ ለነበራቸው ሎሳንቲን በተባለው መድሃኒት አፋቸውን መለቃለቅ ይረዳ ነበር እለዚያ ግን ተሰፋ ያለው ነገርም አልነበረም፡፡

በጥር ሀያ ሰባት ሌሊቱን በዘጠኝ ሰአት አዛዡ ታመዋል ብዬ ተጠራሁ፡፡ ወደ እላቸው ዋሻ እየሄድኩ መንገዱ ላይ እኔ ራሴም የማዞር ሰሜት ተሰማኝ ብርድ ብርድም አለኝ ጉሮሮዬም የማቃጠል ሰሜት ነበረው፡፡ ሰደርስ ተጋድመው ሀይለኛ ትውከት ላይ ነበሩ፡፡ ሆዴንና ጉሮሮዬን ያቃጥለኛል አሉ፡፡ ራሴን ያዞረኛል፤ አይኔም ውስጥ የብርሃን ብልጭታ ይታየኛል ብለው ህምማቸውን ገለጡ፡፡

የተበላሸ ምግብ መሆን አለበት (ፉድ ፖይዝኒንግ) ግን ምን አይነት እና እንዴትስ?

አዛዡ አዲስ ከታረደ ከብት ጥሬ ሥጋ መብላት ይወዳሉ፡፡ ይህን በሽታ የሚያስከትል ሌላ ነገር መኖሩን ማሰብ አልቻልኩም፡፡ የደጃዝማቹን ሆድ እያጠብኩ እያለ አንድ ሰው እየሮጠ መጣና ቄሱ ፈታውራሪ ሙላውና ወጥቤታቸው በተመሳሳይ ህመም እንደሚሰቃዩ ተናገረ፡፡ ቄሱና ፈታውራሪው ማምሻውን እራት አብረውን ነው የበሉት፡፡ ዋና ምግብ የነበረው አዲስ ከታረደው ፍየል ጉበትና ጨጓራ (ዱለት) ነበር፡፡

ወዲያውኑ የወጥ ቤት ሀላፊውን አስጠራሁና ለዚህ ምግብ መመረዝ ምክንያቱን እንዲያብራራልኝ ጠየቅሁት፡፡ እሱም ምንም ማብራሪያ የለውም እንዳው ፍየሎቹ እራሳቸው ካልሆኑ በስተቀር፡፡ ሰናስተውል አሥራ አንዱ ፍየሎች ያን ቀን ማታ ሞተው አድረዋል፡፡ ከዚያ በፊት ግን ሁሉም ደህና ነበሩ፡፡ የመስታርድ ጋዝ መመረዝ ይሆናል የሚል ጥርጣሬ አደረብኝ፡፡ ፍየሎቹ ጋዝ ያረፈበትን ቅጠል በልተው ሊሆኑ ይችላል፡፡

በኋላ ባደረግነው ምርመራ ጥርጣሬየ ትክክል ሆኖ ተገኘ፡፡ በመድሃኒት ሀይል፤ ትውኪያና፤ ባይካርቦኔት በተባለ መድሃኒት ሆድን ማጠብ የነበረኝና ማድረግ የምችለው ነገር ነበር ከዚህ በተጨማሪ ሰውነታችን በማላብ ተሸሎን በእግራችን ተመልሰን መቆም ቻልን፡፡ አዛዡ ግን የሚወዱትን ምግብ በጣም በልተው ሰለነበር ለአምስት ቀናት ያህል ታመሙ፡፡

በየካቲት አስራ እራት መቶ ሀምሳ የሚሆኑ የኢጣልያ ቃኝ ወታደሮች ወደ አዲያቦ አካባቢ መጥተው ነበር፡፡ በእንድ የራስ አምሩ ጦር ክፍል ተከበው አንዳስ ተደመሰሱ፡፡ ከዚህ የተረፉት ሁለት ፖሊሶች(ካረቢኔር) በአሥራ ሰባት ወደ ዳባት እንዲሄዱ በኛ በኩል ተላኩ፡፡ ደጃች እያሌው ደግሞ በጠላት በኩል ያለውን ወይም የሚካሄደውን ማወቅ ፈለጉና ወደ ራሴ መኖርያ አካባቢ ወስጄ ወሬ እንዳውጣጣቸው ጠየቁኝ፡፡

ደስ የሚሉ ወጣቶች ነበሩ ወዲያም ተግባባንና ወዳጆች ሆንን፡፡ በነሱ በኩልም ብዙ ወሬ አገኘሁ፡፡ ራስ ሙሉጌታ በየካቲት አሥራ አንድና እሥራ ሁለት በአምባ እራዶም እንደማይንሰራሩ ሆነው በጣልያን መሸነፋቸውን ሰማሁ፡፡ ራስ ደስታም ቢሆን በዶሎ አካባቢ ተመሳሳይ ዕጣ አጋጥሟቸዋል፡፡ በተጨማሪም እንድ የስዊድን ዶክተር መቁሰሉንና የስውዲን ህክምና እባል የሆነ ሰው መሞቱን ሰማሁ፡፡

ማርሻል ባዶሊዮ በሚቀጥለው ወር ማሰቂያ በሁሉም ግንባሮች ከፍተኛ ማጥቃት ለማድረግ መዘጋጀት ማሰቡን ሰማሁ፡፡ ራስ አምሩንና ደጃች እያሌውን ደግሞ ወደ ሰሰህሰሀ አፍ ጋጋ በር አካባቢ እንዲወጡ አድርጎ ማሰፊያውን ዘግቶ በሀይል ለመድመሰስ መታሰቡን ሰማሁ፡፡



ማርሻል ባዶሊዮ ወረራውን አላፋጠንከም ተብሎ በተመለሰው በማርሻል ዲ ቦኖ ምትክ ወደ ኢትዮጵያ የመጣ ነው፡፡ በኋላ ግን ሞሶሎኒ ከሥልጣን እንዲወርድ ከአደራጁት አንዱ ሲሆን ከዚያም የኢጣልያ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ ነበር

አንደ ጓደኛቸው ስላዩኝ ወደዛ አካባቢ አንዳልሄድ መከሩኝ፡፡ በተቻለ መጠን በርቀት ለመቆየት አንድሞክር ነገሩኝ፡፡ አለዚያ ግን በሀይወት የማልመለስ ለመሆኑ ፍራቻቸውን ገለጡልኝ፡፡

ምንኛ ደስ የሚል ዜና ነው! ከአዲስ አበባና ከአምባ እራዶም በሚመጣልን የሰላም ወሬ ጭምጭምታና የውሸት ሪፖርት እኛ በነበረን የልጅ



አይነት ግዴለሽነት ስናንቀላፋ ከርመናል፡፡ ውነት ነው ለአምስት ቀናት የመድፍ ድምፅ በምሥራቅ አቅጣጫ ስንሰማ ነበር፡፡ አንዳንድም ጊዜም መሬቱ ይንቀጠቀጥ ነበር፡፡ እኛ ግን ያሰብነው ራስ ሙሉጌታ መቀሌን መልሰው ለመያዝ የሚያደርጉት ዝግጅት ነው ብለን ነበር፡፡

ደጃች አያሌው ይህንን ሁሉ መረጃ እንደሰሙ ወደ ራስ አምሩ ሰው ላኩና ለብርቱ ውይይት ራሳቸው ስለሚመጡ አመሻሽ ላይ እንዲጠብቋቸወ ጠየቁ፡፡ ለደህንነት ሊባልም ሀያ አምስት ቀላል አውቶማቲክ መሳሪያና ሁለት ከባድ እውቶማቲክ መሳሪያ በያዙ እምስት መቶ ዘቦች ታጀቡ፡፡ ራሳቸውን ለመጠበቅም አጃቢዎችን በግማሽ ከብ እሰልፈው ከራስ እምሩ ካምፕ ውጭ ቦታ ይዘው ጠበቁ፡፡

የጎጃም ወታደሮች ደግሞ በደጃች አያሌው ዘቦች ረጋ ማለትና በራስ መተማመን ስሜት በጣም ተገርመው እንደነበር ይነገራል፡፡ ዘቦቹ እስከ ሕይወታቸው መጨረሻ ድረስ አያሌውን ለመጠበቅ መዘጋጀታቸው ያስታውቅ ነበር፡፡

ራስ አምሩ በዚያን ጊዜ ከፉ ሀሳብ ነበራቸው ብዬ አላስብም፡፡ ነገር ግን የአቢሲኒያዊን ልብ ማን ያውቃል?

ማታ ስንጠብቅ አመሸን አያሌው እልተመለሱም፡፡ እንግዲህ መጥፎ ነገር ሆኗል ማለት ነው፡፡

በየት አቅጣጫ እንደምሄድ ራሴን ለመጠበቅ ምን ማድረግ እለብኝ የሚል ሃሳብ መምጣቱ ራሱ ያሳሳብኝ ጀመር፡፡ እያሌው በራስ አምሩ ከታሰሩ አመፅና ግርግር እንደሚነሳ ጦሩም እርስ በርሱ መዋጋት እንደሚጀምር ግልፅ ነበር፡፡

ነገር ግን በጠዋት ትዛዝ የያዘ ፈጣን መልከተኛ ከተፍ አለ፡፡ ትዛዙም አመሻሽ ላይ ጠቅላላው ጦር አንቅስቃሴ አንዲጀምርና በእንዳ ስላሴ በዋሻ ከሚቆዩት ከደጃች አያሌው ጋራ አንዲገናኝ የሚል ነው፡፡ የጣልያን ዲቪዚዮን ከአክሱም ተነስቶ ሰሰህለሀን ለመያዝ ማቀዱን ወሬ ስምተዋል፡፡ ደጃዝማች ደግሞ ከጠላት ተጠግቶ ሁኔታዎችን መከታተል ይበጃል ብለው እስበዋል፡፡

በየካቲት ሀያ ሁለት አንድ ወር ከቆየንበት ካምፕ ለቀን ተንቀሳቀስን፡፡ በጨረቃ ብርሃንና በሰፊው መንገድ ስንገሰግስ አምሽተን ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰአት ሲሆን ከአዛዡ ጎን ቁጭ ብያለሁ፡፡ ሲነግሩኝም ራስ እምሩ የወዳጅ ባህሪ ነው ያሳዩት ነገር ግን እኔ ያገኘሁት መረጃ በጭራሹ የገባቸው አይመስልም፡፡ ስለ

ራስ ደስታ መሸነፍ ያለጥርጥር ያውቁ ነበር ስለሌሎቹ ሰዎች ግን ምንም አይነት ቃል መስማት አልፈለጉም::

በሀያ አንድ የበለሳው ፊታውራሪ ነጋሽ የጣልያን ወታደሮች እየመጡ እንደሆነና በሚቀጥለው ቀን ውጊያ መጀመሩ የማይቀር መሆኑን አስታወቁን ሆኖም ግን ቀዳሚው ጦር በቂ የሆነ መከላከል ማድረግ ይችላል ብለው ማስባቸውንም ነገሩን::

ከኛ ጋራ ከተቀላቀሉት ከራስ እምሩ ጋራ በመሆን እመሻሸ ላይ ለውጊያ ጠጋ ማለት እንድንችል ወደፊት መንገድ ትንሽ ገፋ አደረግን:: በዚያ ቦታ የነበረውን ያህል የዋሻዎች ብዛት አይቼ አላውቅም:: በስአታት ውስጥ ወደ ስላሳ ሺ የሚጠጋውን ጦር እንዳለ ዋጥ አደረገው::

ያን ቀን ማታ ምንም አይነት የማበረታታት ሁኔታ የማይሠጥ አንድ ነገር አየን:: ከሀያ አራት ሰአት በፊት ሰፍረንበት በነበሩት ተራሮችና ኮረብታዎች ላይ ወደ አስር የሚሆኑ ቦታዎች ላይ እሳት ይነድ ነበር:: እሳቶቹ ይፈጉና ይጠፉ ነበር ሃበሾቹ እንደሚሉት ርችት መሆኑ ነው::

ያካባቢው ሰዎች አታለውናል:: አሁን ደግሞ ለጣልያኖቹ ስለ መንገዳችን ምልክት እየሰጡ ነበር:: ገበሬዎች በተዘረፈው ቤታቸው ምክንያት ተናደዋል እና በቀላቸውን ግን በጥሩ ሁኔታ በያዝናቸው በኛ ላይ ሊወጡ ነው ምክንያቱም ከበደላቸው ጦር ጋር አብረን ስለምንጓዝ ነው:: ስለዚህ ሌላ ጠላት ደግሞ አፍርተናል:: ወዮ በነዚህ በተናደዱ ገበሬዎች እጅ ለወደቀ ሰው ሀይወቱ የሁለት የምግብ ፍሬ ያክል እንኳን ዋጋ አይኖረውም::

በየካቲት ሀያ ሁለት እሳቱ ምልክት ለመሆኑ አረጋገጥን የጣልያን አውሮፕላኖች የት ቦታ እንዳለን በትክክል አውቀዋል:: በዋሻዎች መግቢያ ላይ ብዛት ያለው ቦምብ ጣሉ:: የአውቶማቲክ መሳሪያ ጥይቶች የዋሻዎች ግድግዳ ላይ ይነጥሩ ነበር:: የእሳት ቦምቦች ደግሞ ሜዳው ላይና በሸለቆው ያለውን የደረቀ ሳር ያጋዩት ነበር:: እንስሳቶች ሳይቀር በዋሻው ውስጥ መጠለያ አግኝተው ስለነበር በዚያን ቀን የደረሰው ጉዳት መጠነኛ ነበር:: እንደሌላው ጦር ሁሉ እኔም እነዚህ ዋሻዎች ለኛ ሲባል ነው የተፈጠሩት ለማለት ከጅሎኝ ነበር:: ለማንኛው አስገራሚ ነበር ደግሞም በሚመች ቦታ ነው ያሉት::

በሀያ ሁለት ከሰአት በኋላ ከኛ ቀዳሚ ጦር ጋራ የሚደረገውን ውጊያ መስማት እንችል ነበር:: ረዳት ጦር ስላልተጠየቀ ቀለል ያለ ግጭት ነበር የመሰለን::



ፀሀይ ስትጠልቅ ከአክሱም ውጭ ያሉትን የጣልያኖቹን የመብራት ምልከቶች ማየት እንችል ነበር:: ቀይ፣ አረንጓዴ፣ ነጭና ቢጫ መብራቶች ወደ ማይል በሚጠጋ ቦታ ላይ ጠቆር ባለ ደመና መሀል ከዚህም ከዚያም ይብለጨለጩ ነበር:: አስደሳች ትዕይንት!

ወደኋላ ማምሻውን የበለላው ፊታውራሪ ነጋሽ የመጨረሻቸውን ውጊያ ማድረጋቸውን ዜና ሰማን:: ግጭቱ የተጀመረው ከቀኑ ስምንት ሰአት ነበር:: ነጋሽ እንደተራ ወታደር በግንባር ሆነው ጥይት ይተኩሱ ነበር:: ከሶስት ሰአታት ተኩስ ልውውጥ በኋላ ጨበጣ ውጊያ ተጀመረ:: በተኩስ ብዛት ሞቆና ቀልቶ ስለነበር የነጋሽ መውዜር ጠመንጃ ደግሞ ነከሰ:: ለወታደሮቻቸው የሚሆን ጥይትም እያለቀ ነበር::

ከዚያም ፊታውራሪ በጩኸት "ልጆች! ከዛፉ ስር የቆመውን ያን ከፍተኛ መኮንን ታያላችሁ? የኔ ነው! እንዳትነኩት"

ጠመንጃቸውን ወርውረው ጎራዴያቸውን መዘው ከወታደሮቻቸው ፊት ለፊት ወደ መኮንኑ ገሰገሱ:: ጥይት በዙሪያቸው ይከንፋል ግን ከጉዳይ አልቆጠሩትም፤ አይናቸው የተተከለው ዛፉ ስር የቆመው ጣልያናዊ ላይ ነበር::

ነጋሽ ለራሳቸው ምንም ሳያስቡ በጠላት ወታደሮች መሀል ሮጡ:: አስር ሜትር ብቻ ይቀራቸው ነበር:: የጦርነት ጥማቸውን በተመረጠው ሰውየ ደም ሊያረኩ ይሆን? የራሳቸው ወታደሮች ተስፋ የለውም ብለው አሰቡ:: ነገር ግን ነጋሽ የነበረውን ችግር አልተቀበሉትም:: በዚያች ወቅት ለሳቸው የጠላት ወታደር ሆነ የጠላት ጥይት አልነበረም ሰውየው ብቻ ነው የታያቸው:: ጥይቶችም ሊነኳቸው የፈሩ አይመስልም ነበር:: ተልኳቸውን እስኪፈፅሙ ድረስ ሕይወታቸውን ሊጠብቁ የፈሩ ይመስል ነበር::

ከኢላማቸው ትንሽ እርምጃዎች እስኪቀሩ ድረስ ባለ ጉልበታቸው ወደፊት ተወረወሩ

አሁን ግን ዛፉ ስር ያለው ሰው ወደሱ የመጣውን ጥቃት ተመልክቷል:: ወዲያውኑ ሽጉጡን መዘዘ:: ነገር ግን ዘግይቷል:: በድንጋጤ የፈዘዙት ጣቶቹ የሽጉጡን ምላጭ ሙሉ በሙሉ ከመሳባቸው በፊት በጀግና እጅ የሚወዛወዝ ደም የጠማው ጎረዴ አንገቱ ላይ ወረደበት:: የመኮንኑ ሰውነት ከመውደቁ በፊት ጭንቅላቱ እግሩ ስር ዘፍ አለ::

ነገር ግን ሽጉጡ ደግሞ ጥይት ተኩሶ ስለነበር የተተኮሰው ጥይት የነጋሽ ልብ ውስጥ ተቀረቀረ:: በዚያን ሰአት ግን ሌሎች አስር ጥይቶች በጎናቸው መቷቸው:: ለዚህ ጊዜ ነበር ወይ ጥይቶቹ የቆዩት? ግን ለምን?

የበለሳው ፊታውራሪ ነጋሽ ስማቸውን አደሱ:: ከመውደቃቸው በፊት እስከመጨረሻዋ ደቂቃ ድረስ አሌ የማይባል ጀግና መሆናቸውን አስመሰከሩ:: ለሁልጊዜም ጀግና እንደሆኑ ይኖራሉ::

ጣልያኖች በቁጥር እጥፍ ቢሆኑም የኢትዮጵያውያኑ ቀዳሚ ጦር ያሉበት ቦታ እንዳይንቀሳቀሱ አድርጓቸዋል:: ጠላት ወደፊት መጓዝ አልቻለም እንዲያውም ስትንሽ ርቀት ወደኋላ ለማፈግፍግ ተገዷል::

አመሻሽ ላይ ወደፊት ተጓዝንና ከአፍ ጋጋ ማለፊያ አራት ኪሎ ሜትር ርቀት ቦታ ደረስን:: በዚያ አካባቢ ያሉ ዋሻዎች ብዛት አልነበራቸውም ግን ሰፋፊ ነበሩ:: ከመሬት በታች የሆነ አንድ ክፍል ውስጥ መጠለያ አደረግን የዚህ መጠለያ መግቢያው መሀል ሜዳ ላይ ከትልቅ ዛፍ ስር ነበር:: ሁለተኛው መግቢያ ደግሞ ወደ ገደል ነው የሚወስደው:: ቦታው ውስጥ የነበርነው ወደ ሁለት ሺ ሰዎች እንሆናለን ግን ክርን ለክርን አልተገፋፋንም:: ፊታውራሪ ሙላውና የራስ አምሩ ፊታውራሪ ከንፈ ፊታውራሪ ነጋሽ የሞቱበትን ቦታ መልሰው እንዲይዙ ታዘዙ::



# ምዕራፍ አሥራ ሰባት

## ቅዱስ ጊዮርጊስ አልጠበቀንም

የካቲት ሀያ ሶስት ነጋ:: የአድዋ ድል አርባኛ አመት ነበር:: እንደዛን ጊዜም ዛሬ እሁድ ነው:: ጨለማን ተገን አድርገው የጠላት ወታደሮች ወደፊት በመጓዝ ጋራውን አቃበ ሰአት፣ አዲ ሀመልማል እና ሰለህለሀን ይዘዋል:: እነዚህ ቦታዎች ደግሞ ጎን ለጎን ነው ያሉት:: ከመጨረሻው ቦታ በምሥራቅ በኩል ደግሞ አዲስ ሬጅመንት በጥዋት ቦታውን ያዘ:: አሁን ከአክሱም በረድፍ የሚመጡ የጭነት መኪኖችን እናያለን:: ተጨማሪ ወታደር ስንቅና ትጥቅ ነው ይዘው የሚመጡት:: እሁኑኑ ለማጥቃት እንዳሰቡ ምንም ምልክት አይታይም::

ከቀኑ ወደ መሀል ላይ በመጣ ዜና ደግሞ ሞተረኛ የሆነ የጣልያን ጦር በመረብ በኩል አድርጎ አዲ አዞ ተሻግሮ እየተጓዘ እንደሆነ ሰማን:: ግልፅ ሆኖ እንደሚታየው ከኋላችን ሆነው ሊያጠቁን ፈልገዋል:: ወይም ደግሞ መሸሻ መንገዳችን ከኋላ በኩል በምዕራብ አድርገው በቆየሳ ተራራ ዙሪያ መዝጋት ፈልገዋል:: ሁለቱ የጣልያን እስረኞች ሳያጋንኑ ለመናገራቸው ይህ በቂ መረጃ ነበር:: እኛን ወደ ወጥመድ ስበው በመክበብ ሙሉ በሙሉ ለመደምሰስ ፈልገዋል::

በሚያስተማምን መልከተኛ በኩል ራስ እምሩና ደጃች አያሌው ሙሉ ቀን መልከት ሲለዋወጡ ዋሉ:: ደጃች አያሌው ጠላት ሳይጠናከር እሁኑኑ ማጥቃት ፈልገዋል:: ውነት ነው ቀኑ ሁለት በአል ነበረው እሁድም እና ቅዱስ ጊየርጊስም ነበር:: ግን ደጃዝማች "በችግር ምክንያት መደረግ ያለበት ነገር ሲኖር ህግና ልምድ አይከበርም" አሉ::

ነገር ግን ራስ እምሩ እርግጠኛ አልነበሩም እና በማታ መንቀሳቀስ ነው የሚሻለው ብለው ነው ያሰቡት:: አለዚያ እንዴት ተብሎስ የአየር ጥቃቱን ማምለጥ ይቻላል? በዚህ እንኳን ውነት ነው ትክክል ነበሩ::